2026-2027

# STUDENT Code OF Conduct in Montgomery County Public Schools

Federal and state laws, Montgomery County Board of Education policies, Montgomery County Public Schools (MCPS) administrative regulations, and other guidelines are subject to change and shall supersede the statements and references contained in this publication.

Student Name ____________________

Phone ____________________

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

## ዕሴት፡-

ትምህርት
መከባበር
መልካም ግንኙነት
ልህቀት/ምጡቅነት
ፍትኃዊነት

## ራእይ፡-

የወደፊት ዝግጁነት፡-
በተለዋዋጭ አለም ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ለእድገት፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ እና ለስኬታማነት ዝግጁ ሆነው ይመረቃሉ—በማህበረሰባቸው ውስጥ እና ከዚያም በላይ ለመሪነት፣ ለአገልግሎት፣ እና በጎ ተጽእኖ ለመፍጠር በሚያስችላቸው እውቀት፣ ችሎታ፣ እና በራስ በመተማመን ተገንብተው ይመረቃሉ።

## ተልእኮ፡-

እምቅ አቅምን በተግባር እንዲገለጥ ማድረግ፥
ሁሉም ተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ፣ ትምህርትን የማዳበር እና የማበልጸግ እድሎችን በመጠቀም ጠንካራ የአካዳሚክ መሠረት ይኖራቸዋል። ሁሉም ተማሪዎች ለውጦችን እና አዳዲስ ሁኔታዎችን መቋቋም የሚችሉ ሆነው ዕድሜ ልክ የመማር ፍላጎትና ጽናትን ያዳብራሉ። ሁሉም ተማሪዎች ትርጉም ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ መስተጋብር፤ ውጤት ላይ የሚያተኩሩ እና በትብብር የሚሠሩ ይሆናሉ። ሁሉም ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ አዎንታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር የተዘጋጁ፤ እና በግል ህይወታቸው እና በሙያዊ ብቃታቸው ለስኬታማነት የሚተጉ ይሆናሉ።


**የትምህርት ቦርድ**
Board of Education

**ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን** Ms. Grace Rivera-Oven
**ፕሬዚደንት** President

**ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ** Ms. Brenda Wolff
**ም/ፕሬዚደንት** Vice President

**ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ** Ms. Rita Montoya

**ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ** Ms. Karla Silvestre

**ወ/ሮ ላውራ ስቲዋርት** Mrs. Laura Stewart

**ሚ/ስ ጁሊ ያንግ** Ms. Julie Yang

**ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን** Ms. Natalie Zimmerman

**አቶ ልዑል ዳዊት** Mr. Leul Dawit
**ተማሪ አባል** Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

**ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)**
**የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት**
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# ማውጫ

የፈጣን ማመሳከሪያ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ክፍል I ፡- ባህሪ እና ስለ ደህንነት እሳቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ክፍል II፡- የባህሪ ማስተካከያ እርምጃ ጣልቃ ገብነት ሜትሪክስ . . . . . . . . . . . . 5

ሰንጠረዥ 1: ሜትሪክስ 6 ላይ የሚተገበሩ የባህሪ ማሻሻያ እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች . . . 6

በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

የተማሪ ባህሪያት እና ጣልቃገብነት የምላሽ አሰጣጥ ደረጃ ሜትሪክስ . . . . . . . . . . . .14

የባህሪ ማሻሻያ እርምጃ ጣልቃገብነቶች እና ትርጓሜዎች . . . . . . . . . . . . . . .27

የተማሪዎች የሥነ ምግባር ደንብ እና የልዩ ትምህርት መስፈርቶች . . . . . . . . . . . .30

የተማሪዎች የሥነ ምግባር ደንብ እና የአማራጭ ትምህርት ፕሮግራም መስፈርቶች . . . . . . . .31

የአፈጻጸም ሂደት ፕሮቶኮል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .32

ስለ ተማሪ ባህሪ የማስተካከል ጣልቃገብነት፣ የት/ቤት ሠላም፣ እና ደህንነትን በተመለከተ የትምህርት ቦርድ "BOE" ፖሊሲዎች እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች . . . . .33

ስለ ፀረ-መድልዎ መግለጫ በጀርባ ሽፋን ገጽ ላይ ይገኛል

(የድርጅት ሠንጠረዥ ሲዘጋጅ እና ሲወሰን የግንኙነት መረጃ ወቅታዊ መሆን እንዳለበት በህግ የተደነገገ ነው)

# ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች ጠቃሚ ግብዓቶችን የያዘ ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ

## በቀውስ ግዜ ክፍት የስልክ መስመር
### 24-ሰዓት መረጃ መስጠት፣ሪፈራል፣ እና በውይይት መርዳት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል
Hotline/EveryMind/ .988 and https://www.every-mind.org/
በይነመረብ ላይ የሚያነጋግሩ ሰዎች ያሉበት እና የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፥ 24 ሰዓት የማወያየት አገልግሎት ይሰጣል።

Montgomery County Crisis Center . . . . . 240-777-4000
ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል
ቀውስ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

Trevor Project . . . . . . . 866-488-7386፣ Text 678 678

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች ድንገተኛ የስልክ ጥሪ መስመር፡-

Youth Crisis Hotline of Montgomery County . . . . .988
በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት 24 ሰዓት በስልክ የማማከር ድጋፍ እና ሪፈራል የምስጢር አገልግሎት ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቤት ደህንነት ክፍል
MCPS Department of School Safety . . . 240-720-3066

MCPS የተማሪዎች ሥነ ምግባር እና አቤቱታዎች
SWC@mcpsmd.org. . . . . . . . . . . . 240-740-3215
MCPS ዲስትሪክት አቀፍ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን የሚመለከት ግንኙነት ሃላፊ። የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ (SCA) ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/ SCA ከትምህርት ቤቶች፣ ከህግ አገልግሎት ክፍል፣ እና ከሌሎች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር የፖሊሲዎችን፣ የደንቦችን እና የመመሪያዎችን አፈፃፀም ወጥነት ለማረጋገጥ ከሰብአዊ የግንኙነቶች ክፍል ጋር በማቀናጀት ይሰራል። ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (ታይትል IX ጾታዊ ትንኮሳ ጭምር) እና ማስፈራራት፣ የልጅ ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻ፣ አድሎአዊነት፣እና የተማሪ ጾታ ማንነት ክስተቶችን በሚመለከት አፈጻጸሙና ትግበራው ወጥነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይሠራል።

MCPS Cyber Safety . . . . . . . . Abuse@mcpsmd.org
MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔተዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline . . . . . . . . . . . . . . . 1-800-843-5678
24/7 ልጆችን ለወሲብ ድርጊት በማባበል የተጠረጠሩትን ሪፖርት ለማድረግ የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች፣የህፃናት ፖርኖግራፊ፣የህፃናት ወሲባዊ ቱሪዝም፣የህፃናት የወሲብ ንግድ፣ለልጆች የሚላኩ ያልተጠየቁ ጸያፍ ቁሶች፣የተሳሳተ/የተጭበረበሩ የተጠቃሚ ስሞች እና አሳሳች ቃላትን ወይም በኢንተርኔት ላይ የሚለጠፉ ዲጂታል ምስሎችን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የሚያገለግል የስልክ መስመር።

Safe Schools Maryland Hotline .833-MD-B-Safe (833-632-7233)
ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ መስመር 24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛ ውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስልክ የሚደውለውን ሰው ማንነት በመደበቅ ስለተፈጠረው ክስተት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች ጋር መረጃ ይጋራል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት-ጥበቃ(መከላከያ) አገልግሎቶች፣
የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ክፍል
(24 ሠዓት ክፍት የስልክ መስመሮች) . . . . . . 240-777-4417
ወይም . . . . . . . . . . . . . . 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል ለማሳወቅ 24/7 ሪፖርት የሚቀበል የስልክ መስመር።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎት 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
በአዋቂዎች ላይ የሚጠረጠር ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 ክፍት የሆነ የስልክ መስመር።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡- 240-773-5400
በልጆችና በጎልማሶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን፣ ሸሽተው፣ የጠፉ ልጆች፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የተጋላጭ አረጋውያን ጥቃት/አደጋ በአዋቂዎች ላይ የሚደርስ በደል፣ እና የተመዘገበ ሪከርድ ያላቸው የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ፡-
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች (ጋንግ) የጥቆማ መስመር። . .240-773-GANG (4264) ወይም
240-773-DRUG (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ህገ-ወጥ እጽ ማዘዋወር/የወሮበሎች ቡድን (ጋንግ) እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ማንነት ሳይገለጽ ጥቆማ ለማቅረብ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership
ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር ተግባራት 240-740-3977
ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx
የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- . . . . . . . . 240-740-3030
የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል ዋና ኃላፊ . 240-740-3100
የልዩ አገልግሎት ድጋፍ ክፍል . . . . . . . . . 240-740-5630
ሰክሽን 504 አስተባባሪ . . . . . . . . . . . . 240-987-8031

## የሞንትጎመሪ አስቸኳይ ላልሆኑ ጉዳዮች መገልገያዎች (ሪሶርሶች)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ አስቸኳይ
ላልሆነ ጥሪ የስልክ መስመር . . . . . . . . 301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ውጭ . . . . . . 240-777-0311

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡-
www.montgomeryschoolsmd.org

አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎችን ለማግኘት፡-

MCPS ፌስቡክ፡- www.facebook.com/mcpsmd

ፌስቡክ ስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . www.facebook.com/mcpsespanol

የማንቂያ/የማስጠንቀቂያ መልክቶች፡-
Alert MCPS . www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ክስተት ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ:-
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . . . 240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር 240-740-2845
Email. . . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

MCPS የማህበረሰብ መረጃ ቢሮ . . . . . . . . 240-740-2837
ቴሌቪዥን፡ MCPS Televisio www.mcpsTV.org; Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36

በድምፅ የተቀረጸ የአስቸኳይ ጊዜ እና
የአየር ሁኔታ መረጃ . . . . . . . . . . . . 301-279-3673

## MCPS ሪሶርሶች የሚገኙበት ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት:-

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ
- MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ
- አትሌቲክስ
- የትምህርት ቦርድ Board of Education
- ጉልበተኝነት፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት
- የአውቶቡስ መስመሮች
- የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት
- የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል
- የግንዛቤ ትምህርት Common Sense Education
- የኮርስ ጥንቅር መግለጫ
- የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety
- የዲፕሎማ መስፈርቶች
- ወሮበሎች (ጋንግ) እና የወሮበሎች ተግባር
- ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ

## MCPS የሪሶርስ ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

- የጥላቻ ዝንባሌ
- የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች
- ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መመሪያ
- LGBTQ ድረ ገጽ
- የምሣ ምግብ ዝርዝር
- የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች
- ፀረ-መድሎአዊነት
- በኦንላይን የመመረቂያ ትምህርት
- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት
- መርኖች እና ደንቦች
- የስነልቦና አገልግሎቶች
- የተማሪ ሠራተኛ አገልግሎቶች
- የልጅ መበደል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማደረግ
- ፍትኃዊ ተሐድሶ
- በት/ቤት የካውንስሊንግ አገልግሎቶች
- የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች
- የትምህርት ቤት ደህንነት
- ፆታዊ ጥቃት
- የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ (Social Media Digital Citizenship)
- ልዩ ትምህርት
- ልዩ ፕሮግራሞች
- ስልታዊ የእቅድ ዝግጅት
- የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ
- የተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መማር - eLearning
- የተማሪ ግላዊነት
- የተማሪ አገልግሎት ትምህርት
- ራስን የመግደል ሙከራን መከላከል
- የሰመር ትምህርት ቤት Summer School
- ታይትል IX/Title IX

# መግቢያ

የተማሪ የስነምግባር ደንብ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች፣ እና ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ስርአት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢን ለመፍጠር የሚተገበር መመሪያ ነው። አዲስ ፖሊሲ አያወጡም፤ ነገር ግን የሜሪላንድን ህግ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን፣ እና MCPS ደንቦችን (ከዚህ በኋላ "ደንቦች" ተብለው የሚጠቀሱትን) መጠበቅ ያለበት ሥነ ምግባር፣ ባህሪ፣ ደህንነት፣ እና የባህሪ ማሻሻያ እርምጃ ጣልቃ ገብነት ጋር በተያያዘ መልክ ይተገበራሉ። ስለ ቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦችን በአጭሩ ያብራራል፣ ነገር ግን ማንኛውም ሰው MCPS ድረ ገጽ ላይ ባለው የፖሊሲዎች እና ደንቦች መመሪያ ውስጥ ሙሉውን የቦርድ ፖሊሲዎች እና የሞንትጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን ማግኘት ይችላል። ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች በጣም የሚያ ስፈልጋቸውን ፖሊሲዎች እና ደንቦች አጭር ማጠቃለያ ለማግኘት፣ እባክዎን የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ስለ ተማሪዎች መብቶች እና ኃላፊነቶች መመሪያ የሚለውን ተጓዳኝ ሰነድ ይመልከቱ።

የተማሪ የስነምግባር ህግ ተማሪዎች MCPS ንብረት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፣ ይህም የትኛውንም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ወይም ሌላ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት/ፋሲሊቲ፣ MCPS በባለቤትነት የሚያ ስተዳድራቸውን ቦታዎችን ጨምሮ፤ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶ ቡሶች እና ሌሎች MCPS በባለቤትነት የያዛቸው፣ የሚያስተዳድራቸው ወይም የሚቆጣጠራቸው ተሽከርካሪዎች፣ እና ንብረቶች/ፋሲሊቲዎች እና/ወይም MCPS የሚደግፋቸው ተማሪዎች የሚሳ ተፉባቸውና የተለያዩ አክቲቪቲዎች የሚከናወንባቸው (ማለትም፡- የመስክ ጉዞዎች፣ ፕሮምዎች፣ ወይም የአትሌቲክስ ውድድሮች)ሁሉ ይመለከታል። ርእሰምምህሩ በምክንያታዊነት ጥፋቱ የተማ ሪዎችን ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል ብሎ ካመነ ወይም የስነ ምግባር ጥፋቱ ከተፈጠረ ወይም ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በትምህርት ቤት እንቅስ ቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ወይም ጣልቃገብነት ይፈጥራል ተብሎ ከተገመተ ከትምህርት ሰአት ውጭ እና ከትምህርት ቤት ንብረት ርቆ የሚፈፀም የተማሪ ጥፋት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰዳል።

የተማሪ የስነምግባር ህግ የመጀመሪያው ክፍል በስቴት እና በፌደራል የስነስርዓት/የዲስፕሊን ፖሊሲዎች ላይ የተመሰረተ የቦርዱ የስነምግባር እና የደህንነት እሳቤ መግለጫ ነው። የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ ሁለተኛው ክፍል የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ስለ መጥፎ ባህርይ ደንቦችን የሚዘረዝር እና ለእያንዳንዱ የባህርይ ማስተካከያ መወሰድ ያለባቸውን የባህሪ ማሻሻያ ጣልቃገብነት እርምጃዎችን የሚጠቁም ሠንጠረዥ ነው። የባህሪ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ሠንጠረዥ/ሜትሪክስ ገጽ 5 ላይ ይጀምራል። በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች ከገጽ 8 ጀምሮ ቀርበዋል። አባሪ ሰነዶቹ ተጨማሪ ደጋፊ መረጃዎችን ይሰጣሉ።

## ክፍል I ስለ ባህሪ እና ደህንነት እሳቤ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ማስተካከል እርምጃ የመውሰድ ጣልቃ ገብነት፣ ደህንነት፣ እና ስለ ደህንነት ጥበቃ ዕቅድ፣ ቦርዱ ለማስተማር እና ለመማር የተዘጋጀ ሥነ ስርአት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን እንደሚጠብቅ ይደነግጋል — የሞንት ጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ለውጤታማ ትምህርት አስፈላጊ የሆኑ አዎንታዊ፣ ሥነ ሥርዓት የሚከበርበት፣ ሥርዓት ያለው፣ ምቹ፣ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎች ይሆናሉ፤ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚያጎለብቱ፤ የተማሪዎችን ስኬት የሚያሳድጉ፤ እና የተማሪዎችን መጥፎ ባህሪ ከመከሰቱ በፊት በተቻለ መጠን የሚከላከሉ አዎንታዊ የትምህርት ቤት ባህሎችን እና ተስማሚ የትምህርት ከባቢዎችን በንቃት ያዳብራሉ።

የዲሲፕሊን ማሻሻል እርምጃዎች እና የባህርይ ተሐድሶ እርምጃዎችን መጠቀም ከሁሉም የሞን ትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) እና ሰራተኞቹ የሚጠበቅ ነገር ነው። የዲሲ ፕሊን ማሻሻል እርምጃዎችን እና የባህሪ ተሐድሶ እርምጃዎችን መጠቀም ተማሪዎች ከስህተቶቻቸው እንዲማሩ እና አዎንታዊ ምርጫዎችን የሚያግዙ ደጋፊ እርምጃዎች ናቸው። አንድ ተማሪ የትም ህርት ቤቱን ፍላጎት ካላሟላ(ች)፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ችግሩን ለመፍታት እና የማሻሻል እድሎችን ለመስጠት ከተማሪው(ዋ) እና ከቤተሰብ ጋር ይሰራሉ። ተግባራዊ የሚደረጉት የዲስ ፕሊን እርምጃዎች በማሳሰቢያ፣ በውይይቶች፣ ወይም በሌሎች ድጋፎች ሊጀምሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን የመጥፎ ስነምግባር ባህሪው ከቀጠለ የበለጠ ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ። እንደየሁኔታው፣ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ኮንፈረንሶችን፣ እገዳን፣ የወላጅ/አሳዳጊ ኮንፈረንሶችን፣ ወይም ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የመሳሰሉ የተማሪ ስነምግባር ማሻሻያ ስልቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ከባድ የስነምግባር ጥሰት በተፈጸመባቸው ጉዳዮች፣ ትምህርት ቤቶች ወዲያውኑ ተማሪው(ዋ) ከመማሪያ ክፍል ወይም ከትምህርት ቤት እንዲገለል/እንድትገለል በማድረግ የበለጠ ጥብቅ የሆነ የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ። ተከታታይ የዲሲፕሊን እርምጃ እና የባህርይ ተሃድሶ እርምጃ ግቦች የተማሪዎችን የትምሕርት እድገት ለመደገፍ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አክብሮት የተሞላበት የመማሪያ አካባቢን ለመጠበቅ እና የዲሲፕሊን እርምጃዎቹ ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ መሆናቸውን ማረጋገጥ ናቸው።

MCPS ሁሉም ሰው — ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች — ሲተባበሩ፣ ሲያከብሩ/ሲከባበሩ እና እርስ በእርስ ሚናቸውን ሲያከብሩ እንዲሁም ሁሉም ሰው ሥርዓት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን ለመጠበቅ በአክብሮት እንዲሰሩ በሚያስችላቸው የጋራ አስተሳሰብ የባህሪ ማስተካከል ጣልቃ ገብነት ልምዶች ላይ አጽንኦት ሲሰጥ እና በማስተማር እና በመማር ላይ ያተኮረ ሲሆን በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ እና ስኬታማ እንደሚሆን ቦርዱ ያምናል። ይህንን ለማሟላት የሚመለከታቸውና የሚከተሉት ሰዎች ሁሉም የድርሻቸውን እንዲወጡ ይጠይቃል።

- ተማሪዎች ለራሳቸው ትምህርት፣ ለግል ባህሪያቸው እና መብቶቻቸውን ስለሚጠቀሙበት መንገድ ሥነስር ዓት የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ድርጊታቸው የሚያስከትለውን የተጠያቂነት ውጤት እንዲቀበሉ፣ እና ለቦርዱ ፖሊሲዎች እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች እና መመሪያዎች ተገዢ እንዲሆኑ ይጠበቃል።
- ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው ስለሚያጋጥሟቸው የባህሪ ስጋቶችን ለመፍታት ከ MCPS ሰራተኞች ጋር በመተባበር መስራት ይጠበቅባቸዋል፣ ይህም በልጆቻቸው የሚመሩ ወይም በልጆቻቸው ላይ የሚፈጸሙ የባህርይና የስነምግባር ድርጊቶችን ያካትታል። ይህ ማለት ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን በት/ቤት በአግባቡ እንዲመሩ እንዲመክሯቸው እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ልክ እንደ ተማሪዎቻቸው ሁሉ እንዲሳተፉ እና ገንቢ በሆነ መልኩ እንዲተባበሩ አወንታዊ፣ ደጋፊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለሁሉም ተማሪዎች ለመማር እና ለማስተማር ምቹ የሆኑ የት/ቤት ከባቢዎችን ለመፍጠር እና ለመጠበቅ ይረዳል ማለት ነው።
- የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የሚጠበቅባቸውን አወንታዊ ባህሪ መጠበቅ አለባቸው፤ እንዲሁም ለተግባራዊ የትምህርት አሰጣጥ አስፈላጊ ሆነው መከባበር የሠፈነበት አካባቢ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። ሰራተኞች የተማሪን ባህሪ ለመምራት እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለመጠበቅ ተገቢውን የአዎንታዊ ባህሪ-የጣልቃ ገብነት ስልቶችን እና ድጋፎችን መጠቀም አለባቸው።
- አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ የተማሪ ባህሪ በመማሪያ አካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳድር ወይም የመማሪያ አካባቢውን ደህንነት እና ሠላም ሲያደናቅፍ፣ ከቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድልዎ አልባ፣ ፍትሃዊ፣ እና የብቃት ባህል ጋር በሚጣጣም መልኩ ተመጣጣኝ፣ ለተማሪዎች የትምህርት እድገት ተስማሚ፣ ወጥነት ያለው፣ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ ውጤቶችን በመጠቀም ሰራተኞች ጣልቃ መግባት አለባቸው።
- የሜሪላንድ ህግ MCPS ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ እድል የሚሰጥ፣ በባህሪያቸው የሚደርስባቸውን ጉዳት እንዲያርሙ እና በባህሪያቸው ምክንያት የተበላሹ ግንኙነቶችን ወደነበረበት እንዲመለሱ የሚያደርግ ግንኙነትን የማሻሻል የስነስርዓት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል። ይህ ማለት፡-
  - » የማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ዋና ዓላማ ለባህርይ ማሻሻል፣ ለባህርይ ተሓድሶ የሚጠቅም እና ትምህርታዊ ነው፤
  - » ዘዴዎቹ/ስልቶቹ በዋናነት ቅድመ ጥንቃቄ የተሞላበት እና መጥፎ ባህርይን አስቀድሞ ለመከላከል መሆን አለባቸው፤
  - » ግንኙነቶችን ማደስ እና የሚጠበቅባቸውን በመከወን ላይ አፅንዖት ይደረጋል፤ እና
  - » ለደረሱ ጉዳቶች እርምጃ የመውሰድ ተጠያቂነት ይኖራል።
- በስቴት ህግ እና MSDE መመሪያዎች መሰረት፣ MCPS ለመማር ምቹ እና የትምህርት ስኬትን የሚደግፍ አወንታዊ አካባቢን ለመጠበቅ የተነደፉ ተገቢ የሆኑ አመቺ ስልቶችን እና ቴክኒኮችን መጠቀምን ጨምሮ ተከታታይ የባህሪ ማስተካከል ጣልቃ ገብነቶችን ይተገብራል።
- ከስቴት ህግ ጋር በማሟለጥ ከትምህርት ክፍል ማስወጣት፣ ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ማገድ፣ እና ማባረር እንደ የመጨረሻ አማራጭ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

..

በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ፍትሃዊ አፈጻፀም፣ እና የባህል ብቃት፣ አድሎአዊነትን አይታገስም። ይህ የሞንትጎምሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ለሁሉም ተማሪዎችና ሰራተኞች ኃላፊነቱን የመወጣት እና የማህበረሰባችን ፍትሃዊነትን፣ ተሳትፎን፣ እና ተቀባይነትን ለመፍጠር፣ ለማሳደግ፣ እና ለሁሉም ሰው ተቀባይነት ያለው ምቹ እንዲሆን የሚያደርገውን ጥረት ለማሳካት ያለውን አቅም ያደናቅፋል።

## ክፍል II፡- ባህርይ የማስተካከል ጣልቃገብነት ሜትሪክስ

MCPS ተገቢ ባህሪን መማር ለህጻናት የእድገት ሂደት መሠረታዊ መሆኑን ያምናል፤ የተማሪዎችን የተለያየ ባህሪ እና የእድገት ፍላጎቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ደረጃ በደረጃ የማስተካከያ ምላሽ ጣልቃገብነት የሚያሟሉ ስልቶችን የሚጠይቅ መሆኑ ይታመናል። ስለ መማሪያ ክፍል ጣልቃ ገብነቶች (ደረጃ 1)፣ በመማሪያ ክፍል የሚተገበሩ ጣልቃ ገብነቶች እና የድጋፍ ግብዓቶች (ደረጃ 2)፣ ዋና የስነ ምግባር ማስተካከያ ጣልቃ ገብነቶች (ደረጃ 3–5) እና የሱፐርኢንቴንደንት ጣልቃ ገብነቶች (ደረጃ 6) መግለጫዎችን ለማግኘት ከገጽ 6–7 ይመልከቱ። በሚቀጥሉት ገፆች ላይ በሰንጠረዥ የተገለጹት የባህሪ ማስተካከያ ጣልቃገብነት ደረጃዎች በሚከተለው መልኩ መተግበር አለባቸው።

- የተዘረዘሩት የህግ ጥሰቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) የተማሪ ሪኮርዶች መመሪያ ላይ  ከተቀመጡት የዲሲፕሊን ኮዶች ጋር በቀጥታ ይገናኛሉ። ስለ እያንዳንዱ የህግ ጥሰት የተቀመጡት መግለጫዎች የተሟሉ አይደሉም።
- የባህሪ ማስተካከያ ምላሾች ከተማሪ እድገት እና ከእድሜ ጋር የተመጣጠኑ መሆን አለባቸው፤ እና በመጥፎ ባህሪ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች በመደበኛነት፣ በፍትሃዊነት እና ለሁሉም ተማሪዎች የግል ትምህርታዊ እድገት እና የመማር እድሎችን በሚደግፍ መንገድ መተግበር አለባቸው።
- የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች በቀጣይነት የባህርይ ማሻሻል የዲሲፕሊን እርምጃ መተግበር አለባቸው፣ በመጀመሪያ ዝቅተኛውን የእርምጃ ደረጃ በመተግበር መጀመር።
- የባህርይ ተኃድሶ እርምጃዎች በዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎች 1-5 ተግባራዊ እንደሚሆኑ ይጠበቃል እና በሲነርጂ መመዝገብ አለባቸው።
- በዲስፕሊን እርምጃ ደረጃ 1-5 ላይ የዲሲፕሊን ማሻሻያ እና የባህርይ ተሃድሶ እርምጃዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ሳይኖር የተማሪ ከትምህርት የመታገድ እርምጃ ተግባራዊ መሆን የለበትም።
- ሰራተኞች ---ጥረት ማድረግ አለባቸው-
  - » ተማሪዎችን የዲስፕሊን እርምጃ በመቅጣት ረገድ አድልዎ እና አለመመጣጠንን ማወቅ እና ማስወገድ እና የዲሲፕሊን ደንቦችን በተከታታይ፣ እና በፍትሃዊነት መተግበር፤
  - » እያንዳንዱ ሰው ዋጋ ያለው የማህበረሰቡ አባል መሆኑን ማሳየት፣ ለተፈጠረበት እና ለማህበረሰቡ አወንታዊ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ የታመነ፣ እና
  - » ተማሪዎችን ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ማስወገድን እንደ የመጨረሻ አማራጭ ብቻ መውሰድ[1] እና ተማሪዎችን በተቻለ ፍጥነት ወደ መማሪያ ክፍል መመለስ ያስፈልጋል።
- ተገቢ ያልሆነ ወይም የመረበሽ ባህሪ የመጀመርያ ሲሆን፣ የት/ቤት ሰራተኛ መጀመርያ ማገናዘብ ያለበት ከሜትሪክሱ (Matrix) ውስጥ ከሁሉም አነስተኛውን የማስተካከያ ደረጃዎች ወይም የዲሲፕሊን ምላሾች መካከል (አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማስተካከያዎች ወይም የዲሲፕሊን እርምጃዎች ከዝቅተኛ ደረጃ መጀመር) አለባቸው። ሆኖም ግን፣ አንዳንድ ጊዜ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ለተከሰተ የባህሪ ጥሰት ጠንካራ የባህርይ ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ያለባቸው ሁኔታዎች ይከሰታሉ። (በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ገጽ 8 ይመልከቱ)
- የክስተቱ ክብደት በባህሪ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት እርምጃ ሠንጠረዥ/ሜትሪክስ ላይ የሚወሰድ ጠንካራ እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

[1]የሜሪላንድ ህገ ደንብ/ "Code of Maryland Regulations 13A.08.01.11(A)"(6)

| ሠንጠረዥ 1፡ ከሜትሪክሱ ላይ በተግባር የሚውሉ የባህሪ ማሻሻያ ጣልቃገብነት ደረጃዎች | |
|---|---|
| ደረጃ 1 | **በክፍል- ውስጥ በአስተማሪ የሚወሰድ እርምጃ**<br>መምህራን በክፍል ውስጥ እና በተማሪ መደበኛ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ተገቢውን ባህሪ ለማስተማር እና ለማጠናከር የማስ ተማሪያ ቴክኒኮችን እና የባህርይ አያያዝ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲማሩ እና ለአስተማማኝ የትምህርት አካባቢ አስተ ዋፅዖ እንዲያበረክቱ፣ በእውቀት እንዲበለጽጉ፣ እና ለተማሪ ማህበረሰቡ ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸው በሚወስዱት የስነምግባር እርምጃ ያበረታታሉ።<br>ስትራቴጂዎቹ እንደ እድሜ ደረጃ እና የእድገት ደረጃቸው ተስማሚ የሆኑ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-<br>• ወደ ባህርይ ተሃድሶ ደረጃ 2 የዲሲፕሊን እርምጃ ከመድረሳቸው በፊት የማስተካከያ እርምጃዎች (በመማሪያ ክፍል) ደረጃ 1 የዲስፕሊን እርምጃ መወሰድ አለበት።<br>• የቃል ማስጠንቀቂያ፣ ማሳሰቢያ/አቅጣጫ ማስቀየር፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ/ይቅርታ፣ ሚና መጫወት፣ የዕለት ተዕለት እድገት ሪከርድ ማድረግ።<br>• ማገጃ መጠቀም።<br>• ወላጅን/አሳዳጊን ማግኘት (በስልክ፣ በኢሜል፣ ወይም በጽሑፍ ወላጅ/አሳዳጊን ማነጋገር) ለመወያየት፣<br>• እንደ አግባቡ—<br>» ተማሪው(ዋ) ከትምህርት ቀን ውጭ ያጋጠሙ ልምዶች እና ከክፍል ተግባራቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ነገሮች፣<br>» እስካሁን የተተገበሩ እና ወደፊትም የሚቀጥሉ ስልቶች<br>» መደበኛ ያልሆነ እና/ወይም በመከላከል ላይ የተመሰረተ የትምህርት ቤት ማማከር፣ እና<br>» በትምህርት ቤት የግጭት አፈታት ዘዴ።<br>• ወደ ካውንስለር ወይም የተማሪ ደህንነት ቡድን ማስተላለፍ። |
| ደረጃ 2 | **በክፍል ውስጥ - በመምህር የሚሰጥ የምክር እና የድጋፍ መርጃዎች**<br>መምህራን ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በክፍል ውስጥ እና በተማሪ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ባህሪን ለማረም የማስተማሪያ ቴክኒኮችን እና የባህሪ ማስተካከያ  ስልቶችን በማስተባበር ያሳትፋሉ፣ በዚህም በሌሎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ፣ ለትምህርት ማህበረሰቦች እና ለተማሪ ትምህርት ተጠያቂ መሆንን አፅንዖት ይሰጣል። ሰራተኞች ድጋፍ ሰጪ መገልገያዎችን/ሪሶርሶችን በማገናዘብ ችግር ያለባቸውን ባህሪያት የሚመለከቱ ነገሮችን ለማቃለል ይጥራሉ።<br>ደረጃ 2 ላይ የሚወሰዱ የእርምጃ ስልቶች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ይጨምራሉ፡-<br>• (በአስተማሪ ውሳኔ) ሁሉንም የደረጃ 1 አማራጭ እርምጃዎች መተግበር<br>• የወላጅ/የአሳዳጊ እና የተማሪ ኮንፈረንስ (ከአስተማሪ እና/ወይም ከድጋፍ ሰራተኞች ጋር)።<br>• የባህሪ ተሃድሶ እርምጃዎች (በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወይም በባህርይ ማስተካከያ እርምጃ አማካሪ፣ ባለሙያ፣ ወይም ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች) ወደ ደረጃ 3 የዲሲፕሊን እርምጃ ከመሄዳቸው በፊት ደረጃ 2 ተግባራዊ ማድረግ እና እንዲመዘገቡ ይጠበቃል።<br>• የትምህርት አስተዳደር ቡድን ኮንሰልቴሽን<br>» ተግባራዊ የስነ ምግባር ግምገማ/የስነ ምግባር ማስተካከያ እቅድ<br>» የስነምግባር ስምምነት መፈረም<br>» የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት<br>» ከትምህርት ቤት ካውንስለሮች/የሪሶርስ ስፔሻሊስቶች ጋር በተወሰነ እቅድ መገናኘት<br>» ወደ MCPS ወይም የማህበረሰብ ሪሶርሶች ማስተላለፍ |
| ደረጃ 3 | የት/ቤት ርእሰመምህር (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚተገበር ዲሲፕሊን)<br>ርእሰ መምህራን በሌሎች ወይም በተማሪ ማህበረሰብ እና በተማሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ስለመጠገን፣ ስለ ተማሪ ተጠያቂነት አፅንዖት ሰጥተው ለመነጋገር ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ደጋፊ ሰራተኞችን ያሳትፋሉ። የባህሪ አያያዝ ስልቶች ተማሪን በመደበኛ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ለማቆየት የሚደረግ ጥረት ቢሆንም፤ ነገር ግን የግዴታ ከሆነ ተማሪን ከክፍል ውስጥ ለአጭር ጊዜ ማስወገድ እና በተቻለ ፍጥነት ወደ መማሪያ ክፍል መመለስ ያስፈልጋል። ደረጃ 3 ላይ የሚወሰዱ ምላሾች ከሚከ ተሉት ስልቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ተግባራዊ ይደረጋሉ።<br>• ደረጃ 1 እና 2 አማራጮች በሙሉ (በርዕሰ መምህር ውሳኔ)<br>• ስለ ጉዳዩ ለመወያየት የወላጅ/የአሳዳጊ እና የተማሪ ኮንፈረንስ ማድረግ (ከርዕሰ መምህር ጋር) —-<br>» በደረጃ 2 ላይ ከተብራሩት አማራጮች ውስጥ ማናቸውንም<br>» በተወሰኑ ጊዜያት ወደ ርዕሰ መምህር፣ ወደ ትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ ወይም ወደ ሪሶርስ ባለሙያዎች መቅረብ፣ እና<br>» የመምህር፣ ተማሪ፣ የወላጅ/አሳዳጊ ኮንፈረንስ።<br>• የስነ ምግባር ማሻሻያ እርምጃዎች (በትምህርት ክፍል ውስጥ የሚከናወን ወይም የባህርይ ማስተካከል እርምጃ አወሳሰድ በሚያሠለጥን ባለሙያ፣ በስፔሻሊስት ወይም በሌላ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ አማካይነት) ደረጃ 4 የዲሲፕሊን እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ደረጃ 3 ተግባራዊ ማድረግ እና የተወሰደውን የእርምት እርምጃ እንዲመዘገቡ ይጠበቃል።<br>• የጉዳት ካሳ<br>• በጊዜ ገደብ የተወሰነ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዳይሣተፍ/እንዳትሣተፍ ማድረግ።<br>• በት/ቤት የሚከናወን የጣልቃ ገብነት እርምጃ።<br>• ከት/ቤት እንዲታገድ/እንድትታገድ ማድረግ።<br>• ለአንድ ቀን ማገድ እና ከተማሪው(ዋ) እና ከወላጅ ጋር እንደገና የመግቢያ ስብሰባ ማድረግ። |

| ሠንጠረዥ 1፡ ከሜትሪክሱ ላይ በተግባር የሚውሉ የባህሪ ማሻሻያ ጣልቃገብነት ደረጃዎች | |
|---|---|
| ደረጃ 4 | **በርዕሰ መምህር የሚወሰን (የአጭር ጊዜ የዲሲፕሊን እርምጃ)**<br>ርእሰ መምህራን የተማሪ ተጠያቂነትን አስፈላጊነት አፅንዖት በመስጠት ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ደጋፊ ሰራተኞችን በማሳተፍ ውይይት ማድረግ እና በሌሎች ላይ ወይም በተማሪ ማህበረሰብ እና በተማሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እንዲጠገን ማድረግ። የባህሪ አያያዝ ስልቶች ትግበራ ላይ ተማሪን በመደበኛ አካዴሚያዊ ፕሮግራም ውስጥ ለማቆየት ጥረት ይደረጋል፤ ነገር ግን እንደ መጨረሻ አማራጭ ተማሪን ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ሊያስወግዱ እና በተቻለ ፍጥነት ተማሪን ወደ ክፍል ትምህርት እንዲመለስ ማድረግ ይችላሉ።<br>ደረጃ 4 እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ ከሚከተሉት ስልቶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ይተገበራሉ።<br>• ሁሉንም ደረጃ 1፣ 2፣ እና 3፣ አማራጮች። እነዚህ የዲስፕሊን እርምጃ ደረጃዎች ካሉ እና ደረጃ በደረጃ የእርምጃ አወሳሰድ ሠንጠረዥ አካል ከሆኑ ደረጃ 1፣ 2፣ እና 3፣ ላይ የስነ ምግባር ተሃድሶ እርምጃዎች ተግባራዊ እንደሚደረጉ ይጠበቃል።<br>• ተማሪው(ዋ) ደረጃ 3 ላይ የተጠቀሰውን የዲሲፕሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት የዲሲፕሊን ማሻሻል እና የባህርይ ተሃድሶ እርምጃዎችን የሚያሳይ ሪከርድ የተደረጉ ማስረጃዎች መኖር አለባቸው።<br>• የአጭር ጊዜ እገዳ (እስከ 3 ቀናት)። |
| ደረጃ 5 | **በርእሰ መምህር ውሳኔ (የረዥም ጊዜ የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ መውሰድ)**<br>ርእሰ መምህራን የተማሪ ተጠያቂነትን አስፈላጊነት አፅንዖት በመስጠት ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ደጋፊ ሰራተኞችን በማሳተፍ ውይይት ማድረግ እና በሌሎች ላይ ወይም በተማሪ ማህበረሰብ እና በተማሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እንዲጠገን ማድረግ። የባህሪ አያያዝ ስልቶች ትግበራ ላይ ተማሪን በመደበኛ አካዴሚያዊ ፕሮግራም ውስጥ ለማቆየት ጥረት ይደረጋል፤ ነገር ግን እንደ መጨረሻ አማራጭ ተማሪን ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ሊያስወግዱ እና በተቻለ ፍጥነት ተማሪን ወደ ክፍል ትምህርት እንዲመለስ ማድረግ ይችላሉ።<br>የደረጃ 5 እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ ከሚከተሉት ስልቶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ይተገበራሉ።<br>• ደረጃ 1፣ 2፣ 3፣ እና 4 ሁሉም አማራጮች። እነዚህ ደረጃዎች ካሉ እና ደረጃ በደረጃ የዲስፕሊን እርምጃ ሠንጠረዥ አካል ከሆኑ ደረጃ 1፣ 2፣ 3፣ እና 4 ላይ ያሉት የባህርይ ተሃድሶ እርምጃዎች ተግባራዊ እንደሚሆኑ ይጠበቃል።<br>• አንድን ተማሪ በደረጃ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ከመወሰናቸው በፊት የማሻሻያ ዲሲፕሊን እና የስነምግባር ተኃድሶ እርምጃዎች መወሰዳቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መኖር አለባቸው።<br>• የረጅም ጊዜ እገዳ (4-10 ቀናት). |
| ደረጃ 6 | **በሱፐርኢንቴንደንት/በተወካይ የሚወሰን የድስፕሊን እርምጃ**<br>እነዚህ የድስፕሊን እርምጃዎች አንድን ተማሪ ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በማስወገድ ከ11-44 ቀናት የሚቆይ እገዳ ወይም ለ 45 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ መባረርን ያስከትላል (ደረጃ 6)።<br>ደረጃ 6 የዲሲፕሊን እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ደረጃ በደረጃ የተወሰዱ  የዲሲፕሊን እና የባህርይ ተሃድሶ እርምጃዎች ደረጃ 1-5 መመዝገብ አለባቸው።<br>ከትምሕርት ቤት ለተራዘመ ጊዜ የማገድ ወይም የማባረር ውሳኔ ለመስጠት በሜሪላንድ ሕግ ላይ የተገለጹትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡—<br>• በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ አደጋ/ስጋት ከተፈጠረ፣ ወይም<br>• በትምህርት ቀን ውስጥ ተማሪው(ዋ) የፈጠረ(ች)ው ከፍተኛ እንቅፋት በሌሎች ተማሪዎች የትምህርት ሂደት ላይ ሥር የሰደደ እና ከፍተኛ መስተጓጎል በሚያስከትል ሁኔታ የተሰማራ ሲሆን ሌሎች ተገቢ የስነምግባር እና የዲሲፕሊን እርምጃዎችና ጣልቃገብነቶች ተገብረው የተሟጠጡ ከሆነ፣<br>• ሱፐርኢንቴንደንቱ/ተወካዩ የእገዳውን ጊዜ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ መገደብ አለበት፤ እና<br>• MCPS ለተገለለ(ች)ው ተማሪ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት —<br>» ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶችን እና<br>» የተማሪው(ዋ)ን በተሳካ ሁኔታ ወደ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እንደሚመለስ/እንደምትመለስ ለማረጋገጥ ተገቢ የባህሪ ድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት3<br>ከባድ ጉዳት የማድረስ አደጋ ማለት፡- የተማሪ(ዋ) ባህሪ ለተማሪ ወይም ለሌሎች ሰዎች ከባድ የአካል ጉዳት የማድረስ እድል ያለው እና ጉልህ የሆነ አደጋ የሚፈጥርበት ሁኔታ ማለት ነው። ከባድ የሰውነት ጉዳት (ከባድ የአካል ጉዳት) ማለት፡- በሰውነት ላይ ወይም በአካላዊ ተግባር ላይ የሚደርስ ከባድ የአካል ጉዳት ሲሆን ይህም ሰፊ ሕክምና ወይም የሆስፒታል ህክምና የሚያስፈልገው በውጫዊ አካል  ወይም ኃይል ሲፈጸም ነው። እንደዚህ አይነት አካላዊ ጉዳቶች ከፍተኛ የሞት አደጋን፣ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ የሆነ የአካል ክፍልን ማሰናከል፣ የአካል ክፍል መጉደል ወይም የአእምሮ ጉዳት፣ ወይም ጥቅም ማጣት፣ ራስን መሳት፣ የአካል መበላሸት እና/ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የአካል ህመምን የሚያካትቱ ናቸው። |

# በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

**የእኔ ተማሪ እርዳታ ማግኘት የሚችለው/የምትችለው ከየት ነው?**

ለሁሉም ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹ እና ደጋፊ የትምሕርት ቤት ድባብ ለመጠበቅ፣ ተማሪዎችም ሆኑ ወላጆች ድጋፍ ለማግኘት የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ፣ ካውንስለር፣ ወይም የሚያምኑትን ሰራተኛ ማነጋገር ይችላሉ።

**ርእሰ መምህሩ ወይም መምህሩ በሠንጠረዡ/ሜትሪክሱ ላይ ከተገለፀው ያነሰ የባህርትይ ማስተ ካከል ጣልቃ ገብነት ደረጃ መጠቀም ይችላሉ?**

አዎ። ሁኔታዎች ከተስተካከሉ የተፈፀመው ስህተት ሁኔታ ታይቶ የድስፕሊን እርምጃ ደረጃን ሊቀንስ ይችላል። የስነምግባር ማስተካከያ እርምጃ መስፈርቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ—

- የተማሪው(ዋ) ዕድሜ፣
- የስነ ምግባር ጥሰቱ በሌሎች ላይ ስላሳደረው ተጽእኖ እና የተማሪው(ዋ) የግንዛቤ ደረጃ፣
- ያልታወቁ ወይም የተደበቁ የትምሕርት ፍላጎቶች ወይም በተማሪው(ዋ) ሕይወት ውስጥ ለሥነ ምግባር ጥሰት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች፣ እና/ወይም
- ስለ ተማሪው(ዋ) ባህሪ ለመረዳት ፍንጭ ሊሰጡ የሚችሉ ባህላዊ ወይም የቋንቋ ምክንያቶች ካሉ።

የባህሪ ጣልቃገብነት አላማ የተጎዱትን ግለሰቦች ለመደገፍ ሲሆን በሌሎች ላይ ጉዳት ያደረሱ ተማሪዎች ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ እና ያደረጉትን ጉዳት እንዲገነዘቡ እና እንዲረዱ፣ እና የሚማሩትን ማህበረሰብ ለመፍጠር እና ለመንከባከብ አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማበረታታት ነው። ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ እድል ይሰጣቸዋል።

**ርእሰ መምህሩ እርምት ለመውሰድ ከፍ ያለ የስነ ምግባር ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃ መጠቀም የሚችለው መቼ ነው?**

ሁኔታዎችን የሚያባብሱ ስህተቶች ጥፋትን ሊያቀጣጥሉ ወይም የበለጠ ከባድ ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ስለዚህ ከፍ ያለ የቅጣት እርምጃ ሊተገበር ይችላል። በሜሪላንድ ህግ የሚጠበቀው የባህሪ ማረም እርምጃ መውሰድ/ጣልቃገብነት ተማሪዎችን በትምህርት ክፍል ውስጥ ማቆየት እና ከትምህርት ቤት እና ከመደበኛ የትምህርት መርሃ ግብራቸው ጋር ተቆራኝተው እንዲቆዩ ለማድረግ ቢሆንም፣ በሜሪላንድ ህግ መሠረት ርእሰ መምህራን የዲስፕሊን ርምጃን የመወሰን ኃላፊነት እንዳላቸው ይገልጻል። ርእሰ መምህራን የተማሪዎችን ባህርይ ማሻሻያ ዲሲፕሊን እና የባህርይ ተኃድሶ እርምጃዎች ተግባራዊ ከተደረጉ እና ማስረጃ ከቀረበ በኋላ ከፍተኛ ደረጃ ያለው እርምጃ የመውሰድ ስልጣን አላቸው። ርእሰ መምህራን ከዚህ በታች ያሉትን ስለሚያ ባብሱ ሁኔታዎችና መስፈርቶች ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፦

- ቀደም ሲል የተፈፀሙ ጥፋቶች ብዛት እና ውጤታማ እንዳልሆኑ የሚቆጠሩ የባህሪ ማሻሻያ የዲሲፕሊን እርምጃዎች።
- በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ዛቻ።
- ከሌላ ጥፋት ጋር በጥምረት የተከሰቱ እኩይ ተግባራት።
- የትምህርት ሂደትን/አሠራሮችን የሚያደናቀፍበት ሁኔታ።
- በስነምግባር ጉድለት ባህሪ ምክንያት የደረሰ ወይም የሚደርስ ጉዳት።
- ፀያፍ ቋንቋን መጠቀም ወይም ጥላቻን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት/ማሰራጨት።

ርእሰ መምህራን ሠንጠረዡ/ሜትሪክሱ ላይ ከተጠቀሰው ዝቅተኛ ደረጃ በላይ ወይም በታች በሆነ ደረጃ የድስፕሊን ቅጣት  እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ መምሪያ (DLSI) የአካባቢያቸው ተባባሪ ሱፐርኢንቴንደንት ጋር መነጋገር አለባቸው። መወሰድ ያለበት እርምጃ ወደ መታገድ ወይም መባረር ደረጃ የሚያደርስ ከሆነ ገጽ 8 ይመልከቱ።

በተጨማሪምጥላቻን የሚያበረታቱ ቋንቋዎችን መጠቀም ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክ ቶችን ማሳየት እንደ ሳይበር ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት ወይም የንብረት ውድመትን ጭምር፣ ወይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ረብሻና ማደናቀፍ እንደሚያስከትል በሚታሰብባቸው ክስተቶች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃን ከፍ የሚያደርግ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል ቦርዱ መመሪያ ሰጥቷል። እነዚህ በቦርድ ፖሊሲ ACA ስለ ፀረ-መድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ውስጥ በተገለጹት የግል ባህሪያት ላይ በመመስረት ፀያፍ ቋንቋን ወይም ምስሎችን እና/ወይም መድልዎን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችንና መግልጫዎችን መጠቀም፣ የዘረ ኝነት ስድብን ጭምር ሊያካትቱ ይችላሉ።

**በቅደምተከተል የሚወሰድ የባህርይ እርምትና ተግሣጽና እርምጃ ምንድን ነው?**

በቅደምተከተል የሚወሰድ የባህርይ እርምት ተግሣጽና እርምጃ ማለት፡- የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪዎችን የባህሪ ችግሮች ለማረምና ለማስተካከል በተዋቀረ ቅደም ተከተል የሚወስዷቸው የዲሲፕሊን እርምጃዎች ሲሆኑ እነዚህም የተሻለ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት እና ችግሮችን ለመፍታት የሚከናወኑ ተግባሮች ናቸው። በቅደምተከተል የሚወሰድ የባህርይ እርምትና የተግሣጽ እርምጃ ዓላማው በቀጥታ ወደ ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ ከመሄድ ይልቅ ማስጠንቀቂያ እና ጎጂ ባህርይን የማሻሻል እድል በመስጠት የስነ ምግባር ጥሰትን ማረም ነው። የትግበራ ሂደቱ በአጠቃላይ በቃል ማስጠንቀቂያ ሊጀምር ይችላል፣ ከዚያም የጽሑፍ ማስጠ ንቀቂያ፣ የስነምግባር ጉድለትን በሚመለከት ለመነጋገር የወላጅ ስብሰባዎችን ማድረግ፣ ከትም ህርት ቤት ማገድ፣ እና በመጨረሻም የስነምግባር ጥሰት ባህሪው ከቀጠለ ከትምህርት ቤት ማባረርን ያስከትላል። ትምህርት ቤቶች እንደ ጥፋቱ የክብደት ሁኔታ የተወሰደው እርምጃ በሰነድ የተመዘገበ እና ፍትሃዊ ሂደትን የተከተለ ከሆነ በሚመለከተው ፖሊሲ ላይ በመመ ስረት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማሻሻል ወይም ከፍ ያለ የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ መውሰድ ይችላሉ፣።

**የስነምግባር ተሐድሶ እርምጃዎች ምንድናቸው?**

የስነምግባር ተሃድሶ እርምጃ አፈጻጸም ከሁሉም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ትምህርት ቤቶች (MCPS) እና ከሰራተኞች የሚጠበቅ ተግባር ነው። የስነምግባር ተሃድሶ እርምጃ አፈጻጸም መልካም ግንኙነቶችን፣ ተጠያቂነትን፣ ጉዳትን በመካስ፣ እና የባህርይ ማሻሻልን አጽንኦት በመስጠት አወንታዊ የትምህርት ቤት አውድ እና የተማሪ ማህበረሰብን መልካም ግንኙነት ለማጎልበት የሚያስችሉ የአስተሳሰብ እና የስትራቴጂዎች ስብስብ ናቸው። የስነምግባር ተሃድሶ እርምጃ አቀራረቦች ከስህተቶች መማርን፣ ግንኙነቶችን በማደስ ወደነበ ረበት መመለስን እና የተማሪዎችን ደህንነት መጠበቅን ያበረታታሉ። ከሜሪላንድ ስቴት የትም ህርት መምሪያ ኮድ 7-306 የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ ጋር በሚጣጣም መልኩ ከዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ጋር በተሳለጠ መልኩ ይተገብራሉ።

ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ዋና አላማው የስነምግባር/ባህርይ ተሐድሶ፣ የማገገም፣ እና ትምህርታዊ እንዲሆን የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል። ስለ አንድ ሰው ድርጊት ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚወሰድ ቁልፍ እርምጃ ስለሆነ የስነ ምግባር ተሃድሶ እርምጃ የት/ቤቶችን ደህን ነትን ለመጠበቅ ካለው ቁርጠኝነት ጋር በምንም መልኩ አይጋጭም። የተማሪ የስነምግባር ደንብ ተማሪ ማህበረሰቦችን ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ እና አንድ ሰው ሲጎዳ በተሐድሶ ወደነበ ረበት እንዲመለስ ማድረግን ይመለከታል። ተገቢ ውጤቶችን ለማግኘት የስነምግባር እርምጃዎች አፈጻፀም 1-5 በደረጃ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ይጠበቃል። ከገጽ 29–31 ያለውን የባህሪ ማስተ ካከያ እርምጃ ጣልቃገብነት ዝርዝር ይመልከቱ።

**በአውቶቡስ ጉዞ ላይ ለሚፈፀምየተማሪ የስነምግባር ደንብ ጥሰት የቅጣት እርምጃ ይወሰዳል?**

አዎ። የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ ተማሪዎች በማንኛውም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ንብረት ላይ ሲሆኑ ማለትም፡- አውቶቡሶችን እና MCPS የያዛቸው፣ የሚያስተዳድራቸው ወይም የተከራያቸው ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ሁሉ ያካትታል።[4]

የተማሪ የሥነ ምግባር ደንብ እና/ወይም የአውቶቡስ ደህንነት ደንቦችን የሚጥሱ ተማሪዎች በሚከተሉት ሂደቶች መሠረት በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ውሳኔ ለጊዜው ወይም በቋሚነት በትምህርት ቤት አውቶቡስ የመጠቀም መብቶችን ሊነፈጉ ይችላሉ፡- (1) የአውቶቡሱ አሽከ ርካሪ በትምህርት ቤት አውቶቡስ ውስጥ ከተሳፈረ(ች) ተማሪ ጋር በተያያዘ የዲሲፕሊን ችግር ሲያጋጥም MCPS ቅጽ 555-3፣ በትምህርት ቤት አውቶቡስ የዲሲፕሊን ግድፈት/ጥሰት ሪፖርት በመጠቀም ጉዳዩን ሪፖርት ያቀርባል/ታቀርባለች። (2) በትምህርት ቤቱ የተወሰደው እርምጃ የዲሲፕሊን ችግሮቹን ካልፈታ የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ተጨማሪ የቅጣት እርምጃ ለማስወሰን ወደ MCPS የትራንስፖርት መምሪያ ክላስተር ተቆጣጣሪ ያቀርባል/ታቀርባለች።

**ተማሪ ከትምህርት ቤት ውጭ ለሚያደርገው የስነምግባር ጉድለት የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድበ(ባ) ት ይችላል?**

አዎን። ከ MCPS ንብረት ውጭ የሚፈፀም የተማሪ ጥፋት ከት/ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ካለው፣ በአካልም ሆነ ቨርቹዋል የትምህርት አካባቢ ቢሆንም፤ ምግባሩ የሌሎችን ተማሪዎች የመማር ሁኔታ የመጉዳት አደጋ የሚፈጥር ከሆነ፣ ወይም ድርጊቱ የትምህርት ሥራን የሚያ ደናቅፍ ከሆነ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

**አንድ ተማሪ ከክፍል ሊባረር የሚችለው መቼ ነው?**

ተማሪዎችን ከትምህርት ክፍል ውስጥ ማስወጣት እንደ መጨረሻ አማራጭ ብቻ ተግባራዊ መሆን አለበት፤ ቢሆንም ግን ተማሪዎች በተቻለ ፍጥነት ወደ መማሪያ ክፍል መመለስ አለባቸው ተብሎ ይጠበቃል። "ማስወገድ" ማለት አንድ ተማሪ ራሱ(ሷ)ን መቆጣጠር የሚች ልበት/የምትችልበት የጥሞና ጊዜ፣ ጊዜያዊ እገዳ፣ ወደ ርዕሰ መምህር ቢሮ ማቅረብ ወይም የበለጠ ከባድ የቅጣት እርምጃ መዘዞችን ሊያስከትል ይችላል። የስነ ምግባር ጥሰት ባህሪው ተደጋጋሚ፣ ረብሻ የሚፈጥር፣ እና በተማሪዎች እና በሰራተኞች የመማሪያ አካባቢ ላይ አደገኛ

[2]የሜሪላንድ ደንብ ኮድ 13A.08.01.11(A)(6) [3]የሜሪላንድ ደንብ ኮድ 13A.08.01.11B(2),(3) [4]MCPS ደንብ EEA-RA፣ ስለ ተማሪዎች መጓጓዣ/ትራንስ ፖርት

ውጥረት የሚፈጥር ከሆነ ተማሪዎች ከክፍል እንዲወጡ ይደረጋል። እባክዎን ስለ “ማስወገድ” በሂደት እንዴት እንደሚስተካከል እና በማን እንደሚተገበር ሠንጠረዡን/ሜትሪክሱን ይመልከቱ።

*ዕረፍት እንዳይወስድ/እንዳትወስድ ሊከለከል ይችላል?*

አዎ። ለምን እና በምን ያህል ጊዜ ተደጋጋሚ እንደሆነ  መታየት ይኖርበታል። MSDE የአካል ማጎልመሻ መመሪያዎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና የእረፍት ጊዜን በመከልከል በተማሪዎች ላይ እንደ የዲሲፕሊን ቅጣት መተግበር እንዳይችሉ ይከለክላል፣ እንዲሁም የቦርዱ ፖሊሲ ለወጣት ተማሪዎች ጨዋታ ለአእምሯዊና አካላዊ እድገት ጥቅም እንዳለው ያረጋግጣል። ሆኖም፣ አንድ ርእሰ መምህር አንድ ተማሪ ልጅ በእረፍት ጊዜ በራሱ(ሷ) ወይም በሌሎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በተመለከተ ምክንያታዊ የደህንነት ስጋቶችን ለመፍታት የሚወስደው እርምጃ "የዲሲፕሊን ግድፈት" ተደርጎ አይቆጠርም።

"ምክንያታዊ የደህንነት ስጋቶችን" የመከላከል እርምጃዎች የሚወሰኑት በርዕሰ መምህሩ ነው። የተማሪው ባህሪ የርእሰመምህሩን/የተወካዩን፣ የካውንስለር፣ የትምህርት ቤቱን የስነ-ልቦና ባለሙያ፣የተማሪ ሰራተኛን ወይም ሌላ ስፔሻሊስትን ትኩረት ሊጠይቅ ይችላል፣ስለ ሆነም እንዲህ አይነት ትኩረት መስጠት ያለበት እርምጃ የሚወሰደው በእረፍት ጊዜም ጭምር ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን፣ በእረፍት ሠአት ከክፍል መውጣት፣ ከጨዋታ፣ እና ከአካላዊ እንቅስቃሴ በተከታታይ የማግለል ሁኔታ አይፈቀድም፣ ይልቁንም በአግባቡ ለተማሪ ድጋፍ የመስጠት ተግባር ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

*ተማሪዎች በቡድን መቀጣት ይችላሉ?*

አይሆንም። በአንዳንድ የቡድን አባላት በሆኑ ተማሪዎች መጥፎ ድርጊት ምክንያት ተማሪዎች በጅምላ የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው አይችልም። ለምሳሌ:- አንድ ተማሪ ክፍል ውስጥ ቢረብሽ በክፍል የሚገኙትን ተማሪዎች በጅምላ በጊዚያዊነትም ቢሆን ማገት አይቻልም። ለጥፋቱ ተጠያቂ መሆን ያለበት ተማሪ ተለይቶ ባይታወቅም ይህ ህግ የፀና ይሆናል።

*አንድ ተማሪ ወይም የክፍል ተማሪዎች በሙሉ በቅጣት መልክ የአካዳሚክ ሥራ እንዲሠራ(ሩ) ማድረግ ይቻላል?*

አይደረግም። አስተማሪ ለመቅጣት ብቻ ተብሎ ስራ የትምሕርት ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ አይቻልም (ለምሳሌ:- ተማሪውን ደጋግሞ እንዲጽፍ ወይም ከመዝገበ-ቃላት እንዲገለብጥ ማድረግ አይችልም)። ይሁን እንጂ አንድ ተማሪ ትምህርት ሊያገኝበት የሚችል ከሆን ከሚወ ስደው ትምህርት ጋር የተያያዘ ጠቃሚ ነገር እንዲማር ሊመደብ ይችላል። የተማሪው ድርጊት በሌላ ተማሪ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳደረ የሚገልጽ ጽሑፍ እንዲጽፍ ማድረግ ተቀባይነት ያለው የአካዳሚክ ተግባር ተምሳሌት ነው።

መቼም ቢሆን የትምህርት ሥራዎች የባህሪ ማስተካከያ እርምጃ አይደረጉም። ነገር ግን፣ ታማኝነት የጎደለው የአካዳሚክ ድርጊት መዘዝ (ለምሳሌ:- የሌላ ሰው የአካደሚክ ሥራ ቀድቶ የራስ ሥራ አስመስሎ ማቅረብ፣ ወይም የአካዳሚክ ሪኮርዶችን መቀየር) MCPS ደንብ IKA-RA፣ ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ በሚለው ዝርዝር ውስጥ ተገልጿል።

*MCPS ኃይል በመጠቀም አካላዊ ቅጣት በመተግበር በተማሪ ላይ የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ መውሰድ ይችላል?*

አይደረግም። አንድ ተማሪ አካላዊ ኃይልን/ጉልበት በመጠቀም ፈጽሞ መቀጣት የለበ(ባ)ትም። ነገር ግን፣ በሜሪላንድ ህግ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ግጭትን ለመበተን፣ ጥቃትን ለመከላከል፣ ወይም የሚረብሽ ተማሪን ለማገታት ምክንያታዊ የሆነ ሃይል ሊጠቀሙ ይችላሉ። MCPS ደንብ JGA-RA የተማሪ ባህሪ ማስተካከያ እርምጃ ጣልቃገብነት እና ደንብ COB-RA ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ ክስተቶች ላይ ከተገለጹት የተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር አካላዊ እገዳን መጠቀም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተከለከለ ነው።

*አንድ ተማሪ ለተመሳሳይ የስነምግባር ጥሰት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊቀጣ ይችላል?*

አዎ። የተማሪ የስነምግባር ጥሰት ባህሪ በተደጋጋሚ የሚከሰት ከሆነ በተደጋጋሚ የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። በተለይም በተከታታይ የሚፈፀም የስነምግባር ጥሰት ወይም ተመሳሳይ ባህሪ ሲኖር የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰዳል። ትምህርት ቤቶች ተደጋጋሚ የባህሪ ጥሰቶችን ቀጣይነት ባለው መንገድ ለመፍታት የሚረዱ እርምጃዎችን እና የባህሪ ጥሰት ማስተ ካከያ ጣልቃገብነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ለአንድ የተማሪ የስነም ግባር ጥሰት አንድ የዲሲፕሊን እርምጃ መወሰድ አለበት፣ ለተለያዩ በርካታ ተመሳሳይ የዲስ ፕሊን ግድፈቶች መሆን የለበትም። የተግሣጽ እርምጃው ተመጣጣኝ፣ የስነምግባር ማሻሻል ለውጥ የሚያመጣ፣ እና በተወሰነ የስነምግባር ጥሰት ባህሪ ክስተት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት (COMAR 13A.08.01)። ትምህርት ቤቶች አንድ ጊዜ ለተፈጠረ ክስተት በተማሪ ላይ በርካታ የዲስፕሊን እርምጃዎችን መውሰድ የለባቸውም።

### አንድ የመማሪያ ክፍል ወይም ትምህርት ቤት የራሳቸውን የሥነ ምግባር ደንቦች መፍጠር ይችላሉ?

አዎን። ተማሪዎች የትምህርት ቤት ወይም የመማርያ ክፍል የሥነ ምግባር ደንቦች፣ የቦርድ ፖሊሲ፣ እና MCPS ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን፣ የስርዓት አቀፍ መመሪያዎችን ጭምር እስካልተቃረኑ ድረስ፣ ለራሳቸው ትምህርት እና ለግል ባህሪያቸው  እንዴት ኃላፊነቱን እንደሚ ወስዱ ለማረጋገጥ የራሳቸውን የመግለጫ ቃላት እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

### MCPS ንብረት ላይ ወንጀል ተፈጽሞ ሪፖርት ሲደረግ ምን ይሆናል?

MCPS የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ወንጀሎችን ለመከላከል (ለምሳሌ:- ዝርፊያ፣ ከውንብድና ቡድን ጋር የተያያዙ የወንጀል ክስተቶች፣ የጦር መሳሪያዎችን መጠቀም ወይም ወደ ትምሕርት ቤት ይዞ መምጣት፣ አስገድዶ የወሲብ ጥቃት መፈፀም) ወይም ሌሎች ከባድ ክስተቶችን (ለምሳሌ:- የቦምብ ማስፈራሪያዎች/ተተኳሽና አጥፊ መሳሪ ያዎች/ፈንጂዎች፣ የእሳት ቃጠሎ/ማቃጠል፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸውና የተከለከሉ አደገኛ ንጥረ ነገሮችን መጠቀም፣ ማሰራጨት፣ የንብረት ውድመት) በተመለከተ ተገቢ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ጋር የመግባቢያ ሠነድ አለው። (ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ደንብ COB-RA፣የአደጋ ክስተት ሪፖርት ማድረግ፣ ይመልከቱ።)

### አንድ ተማሪ ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ንብረት ውጪ በወንጀል ቢሳተፍ/ብትሳተፍ ምን እርምጃ ይወሰዳል?

የተማሪው ጥፋት የተፈጸመው ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ንብረት ውጭ ከሆነ እና በሜሪላንድ ደንብ (COMAR) 13A.08.01.17.A.(8)(c) ውስጥ የተገለጹ የተወሰኑ ወንጀሎችን የሚያካትት ከሆነ፣ ሪፖርት ሊደረግ የሚችል ጥፋት ይሆናል። ሪፖርት ሊደረግ የሚችል ጥፋትን በተመለከተ መታሰር ማለት አንድ ተማሪ MCPS ንብረት ላይ የተወሰነ የጥቃት ወንጀል ፈጽሟል/ፈፅማለች ማለት ነው። የጥፋት ድርጊት በመፈፀም የተጠረጠ ረ(ች) ተማሪ ከታሰረ(ች)በት ቀን ጀምሮ 24 ሰዓት ውስጥ ወይም በተቻለ ፍጥነት የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲው ለትምህርት ቤቶች/ለተወካይ እና ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ማሳወቅ እንዳለበት የሜሪላንድ ሕግ ይደነግጋል። ሪፖርት በተደረገ ጥፋት/የስነምግባር ጥሰት ምክንያት ተማሪው(ዋ) ከመደበኛ የትምህርት ቤት ፕሮግራምና ከትምህርት ቤት ማባረርን፣ ማስወጣት/እገዳ፣ ወይም ሌላ ለውጥ ሊያስከትል ይችላል።

### ተማሪ ሊታገድ ወይም ሊባረር የሚችለው መቼ ነው?

በሜሪላንድ ሕግ መሠረት “ተማሪን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚከናወን እገዳ" (በትምህርት አመት ውስጥ ከ 10 ቀናት ያልበለጠ)፣ “የአጭር ጊዜ” ከትምህርት ቤት ውጭ የሚከናወን ከትምህርት ቤት እገዳ መወሰን (እስከ 3 የትምህርት ቀናት) ወይም “ረጅም ጊዜ” ከትም ህርት ቤት ውጭ የመቆየት እገዳ (ከ 4-10 የትምህርት ቀናት) በርእሰ መምህር ውሳኔ ሊከናወን ይችላል።

ከ 11-44 ቀናት የሚቆይ የተራዘመ ከትምሕርት ቤት እገዳ ወይም ለ 45 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት መባረር (ደረጃ 6) በሜሪላንድ ሕግ የተገለጹትን መስፈርቶች ማሟላት ስላለበት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ እንደሚከተለው ሲወስን ሊተገበር ይችላል:-

1. በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ ዛቻ ከተፈፀመ፤
2. ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቀን ውስጥ ለሌሎች ተማሪዎች መማር እንቅፋት የፈጠረ እና በትምህርት ሂደቱ ላይ ሥር የሰደደ እና ከፍተኛ መስተጓጎል ያስከተለ ሲሆን ሌሎች ተገቢ የሆኑ የስነምግባር ባህሪ ማስተካከያ እና የዲሲፕሊን እርምጃ ጣልቃ ገብነቶች ተሟጠው የተከናወኑ ከሆነ፤
3. ሱፐርኢንቴንደንቱ/ተወካዩ የእገዳውን ጊዜ በተቻለ መጠን ለአጭር ጊዜ ብቻ እንዲሆን ገድበውት ከሆነ፤ እና
4. MCPS ለተገለለ(ች)ው ተማሪ ወደ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በተሳካ ሁኔታ ለመመለስ የሚያስችል ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶችን እና ተገቢ የስነምግባር ባህሪ ማስተካከል ድጋፍ አገልግሎቶችን ሰጥቶ ከሆነ።

በስቴት ህግ መሰረት፣ ከትምህርት ቤት እገዳ እና ማባረር በአጠቃላይ ከቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እስከ 2ኛ ክፍል ለሚማሩ ልጆች በጣም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። የሜሪላንድ ሕግ ከቅድመ-መዋዕለ ሕፃናት እስከ 2ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት በማገድ እና በማባረር ላይ ከፍተኛ ገደቦችን አስቀምጧል። ርእሰ መምህራን/ተወካዮች ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ሠራተኞች በሌላ አይነት የስነምግባር ማስተካከያ እና ድጋፍ በመስጠት ጉዳቱን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል የማያስችል አይቀሬ ከባድ ጉዳትን የሚያስከትል ዛቻ/ስጋት መኖሩን ለመወሰን የት/ቤት የስነልቦና ባለሙያ ወይም ሌላ የአእምሮ ጤና ባለሙያ ማማከር አለባቸው። የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር/ተወካይ የተማሪው(ዋ) ከትምህርት ቤት እገዳ እንዲቀጥል ከወሰነ፣ ውሳኔውን ለማፅደቅ DLSI የሚመለከተውን የትምህርት ስኬት እና የአስተዳደር ዳይሬክተርን ማነጋገር አለበት። የእገዳው ርዝመት ከ 5 የትምህርት ቀናት መብለጥ የለበትም። በፌዴራል ህግ መሠረት ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል ላሉ ህጻናት ከት/ቤት መባረር በውስን ሁኔታዎች ብቻ የተገደበ ነው። MCPS ደንብ JGA-RB ከት/ቤት መታገድ እና መባረር ይመልከቱ።

**በትምህርት ቤት ውስጥ የስነምግባር ባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት (ISI) እና በትምህርት ቤት ውስጥ ከትምህርት እገዳ በማድረግ (ISS) መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረግ የስነምግባር ማስተካከል ጣልቃ ገብነት ደጋፊ እና የባህርይ ማሻሻያ ጣልቃ ገብነት ሲሆን ተማሪው(ዋ) በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ምንም አይነት ከመደበኛ ትምሕርት ፕሮግራም የእገዳ ስያሜ ሳይሰጠው ትምህርት እያገኘ(ች)፣ ሙሉ የትምህርት ቀን ጋር እኩል ያልሆነ ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ፣ ለጊዜው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሌላ ቦታ እንዲቆይ ማድረግ ነው። COMAR በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረግ እገዳን የሚገልጸው አንድ ተማሪ በትምህርት ቤቱ ሕንፃ ውስጥ ካለው የትምህርት ፕሮግራም እስከ 10 የትምህርት ቀናት ድረስ በርእሰ መምህሩ ውሳኔ በዲሲፕሊን ግድፈት ምክንያት ማስወገድ ነው። ተማሪው(ዋ) በአካል ትምህርት ቤት እያለ(ች) ነገር ግን ከመደበኛው የትምሕርት ፕሮግራም ከሚካሄድበት ክፍል እገዳ ማድረግ ነው። ISI እና ISS፣ ትምህርት ቤቶች መደበኛውን ፕሮግራም ለማመቻቸት ተመሳሳይ አገልግሎቶችን እና የባህሪ ማሻሻያ ድጋፎችን መስጠት አለባቸው።

**ከት/ቤት የመታገድ ወይም የመባረር ውሳኔን ይግባኝ ማለት ይቻላል?**

አዎ። ከትምህርት ቤት እገዳ ወይም መባረር ይግባኝ ሊባል ይችላል።

የአጭር ጊዜ ወይም የረጅም ጊዜ ከት/ቤት እገዳ (10 ቀናት ወይም ከዚያ ያነሰ)፦ ወላጅ/አሳዳጊ ልጃቸው 10 ቀናት ወይም ከዚያ ያነሰ ጊዜ ከት/ቤት ከታገደ(ች) ተጨማሪ መረጃዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ብለው ካመኑ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ርእሰመምህርን መጠየቅ ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ያንን መረጃ በኢሜል ወይም በደብዳቤ ወዲያውኑ ለርእሰመምህሩ መላክ አለባቸው። ርእሰ መምህሩ ውሳኔውን እንደገና ካላጤነ፣ ርእሰ መምህሩ የእገዳ ደንቦቹን በትክክል ተግባራዊ እንዳደረገ ለማረጋገጥ ወላጅ/አሳዳጊ የተማሪ ድጋፍ እና ክትትል አገልግሎት ክፍል (DSSAS) ዳይሬክተር የርእሰ መምህሩን ውሳኔ በተገኘው መረጃ ላይ በመመስረት እንዲገመግም ሊጠይቁት ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች DSSAS በሰጠው ውሳኔ ካልረኩ፣ 15 ቀናት ውስጥ የተማሪዎች ሥነ ምግባር እና ይግባኝ ክፍልን በማነጋገር ለሱፐርኢንቴንደንቱ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የይግባኝ መጠየቅ ሂደቱ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ እገዳው ይቀጥላል።

የተራዘሙ እገዳዎች ወይም ከት/ቤት መባረር (ከ10 ቀናት በላይ) ለማባረር የወሰኑት ርእሰ መምህሩ ከሆኑ፣ ሁኔታው እንደገና እንዲታይ የመጠየቅ ሂደቱ ትንሽ የተለየ ነው። ተማሪን 10 የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከትምህርት ለማገድ የሚወሰን ማንኛውም ውሳኔ በተማሪዎች ሥነ ምግባር እና ይግባኝ መምሪያ አማካኝነት መጠየቅ አለበት፣ ይህም እንደ ሱፐርኢንቴንደንቱ ተወካይ ሆኖ ያገለግላል። ተማሪን የማባረር ውሳኔው የተሰጠው ከሱፐርኢንተንደንቱ ከሆነ፣ ወላጅ/አሳዳጊ የሱፐርኢንተንደንቱ ውሳኔ ባለው መረጃ መሠረት ህጎቹን መሰረት ያላደረገ ስህተት መሆኑን ካመኑ፣10 ቀናት ውስጥ በቀጥታ ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

አንድ ተማሪ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት በተለዋጭ የትምህርት መርሃ ግብር ከተመደበ(ች)፣ እንደ ቆይታው ሁኔታ ረዘም ያለ እገዳ ወይም መባረር እንደሆነ ይቆጠራል።

ይግባኙ ከተወሰነው የእገዳ ጊዜ በላይ ሊቆይ እንደሚችል ልብ ይሏል።

**የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሊታገዱ ወይም ሊባረሩ ይችላሉ?**

አዎን። የአፈጻጸም ሂደቶችን ድንጋጌ በመከተል እንዲታገዱ ወይም እንዲባረሩ ስለተወሰነባቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የፌዴራል ህጉ ህጋዊ የአፈጻጸም ዲደቶችን ያስቀምጣል። እነዚህ መብቶች MCPS ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ማገድ እና ማባረር በሚለው ላይ ሙሉ በሙሉ ተዘርዝረዋል።

አንድ ተማሪ ግላዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ወይም 504 ካለው/ካላት እና የትምህርት ቤቱ ቡድን እገዳው እንዲራዘም እና/ወይም ከት/ቤት መባረር ተግባራዊ እንዲደረግ ለመጠየቅ ከፈለገ፣ የተማሪው(ዋ) ባህሪ ሁኔታ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስገድድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን በመጀመሪያ (IEP) መግለጫ ወይም (504) ስብሰባ መካሄድ አለበት። የተማሪው(ዋ) የስነምግባር ባህሪ የሚንፀባረቀው በአካል ጉዳቱ ምክንያት ከሆነ፣ የተራዘመው የእገዳ እና/ወይም የመባረር እርምጃ/ሂደት መቆም አለበት። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን በገጽ 32 ላይ ያለውን የልዩ ትምህርት መስፈርት እና MCPS ደንብ JGA-RC ይመልከቱ።

አንድ ተማሪ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት ወደ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ከተመደበ(ች)፣ MCPS ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት መታገድ እና መባረር በሚለው ላይ ከተገለጸው በስተቀር፣ እንደሁኔታው የተራዘመ እገዳ ወይም መባረር ተደርጎ ይቆጠራል።

**የአፈጻጸም ሂደቱ ምንድን ነው?**

ፍትሃዊ ሂደት ማለት ተገቢ ማሳሰቢያ፣ ጉዳዩን የማድመጥና የማስረዳት እድል፣ እና ሥርዓቱን በትክክለኛ መንገድ መተግበርን የሚመለከት ነው። በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄድ ፍትሃዊ ሂደት ለተማሪው(ዋ) የተከሰሰ(ች)በትን የስነምግባር ጥሰት ማሳወቅ፣ ማስረጃውን ተማሪ ሊረዳው በሚችል መንገድ ማጋራት፣ እና ተማሪው(ዋ) ጉዳዩን በተመለከተ የራሱ(ሷ)ን ታሪክ የመናገርና የማስረዳት እድል መስጠት አለበት። ትምህርት ቤቶች ግኝቶቹን፣ የሚያስከትለውን

መዘዝ፣ እና የዲሲፕሊን ውሳኔያቸውን ምክንያት የሚያብራራ የጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለባቸው። ከትምህርት ክፍል ወይም ከትምህርት ቤት ማስወጣት አስፈላጊ ከሆነ፣ ተማሪዎቹ የትምህርት አገልግሎቶችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች የማወቅ መብት አላቸው። IEP ወይም 504 ያላቸው ተማሪዎች፣ (MCPS ደንብ JGA-RC) መሠረት ትምህርት ቤቶች የዲሲፕሊን እርምጃ ሲተገብሩ የእቅዳቸውን ግቦች እና ዓላማዎች ማሳወቅ አለባቸው።

በሰውነት ላይ የሚደርስ ከባድ ጉዳት (ከባድ የአካል ጉዳት) ምንድን ነው?

በሰውነት ላይ የሚደርስ ከባድ ጉዳት ማለት (ከባድ የአካል መጎዳት) ሰፊ የሕክምና እርዳታ ወይም የሆስፒታል ህክምና የሚያስፈልግ በውጫዊ አካል ወይም በሰውነት ላይ ወይም እንቅስቃሴን የሚጎዳ ከባድ የአካል ጉዳት ነው። እንደዚህ አይነት አካላዊ ጉዳቶች ከፍተኛ የሞት አደጋን፤ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ የሆነ የአካል ክፍል ስንክልና፣ የአካል መጉደል ወይም የአእምሮ ጉዳት፣ ወይም አካላዊ ጥቅም ማጣት፤ ራስን መሳት፤ የአካል መበላሸት እና/ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የአካል ህመምን የሚያ ካትቱ ናቸው።

የሳይበር ጥቃት ምንድን ነው?

የሳይበር ጥቃትት አይነት፣ ግለሰቦች የተለየ ይዘትን እንዲመለከቱ ወይም እንዲያ ሠራጩ ለማድረግ በኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት የሚተላለፍ ሆን ተብሎ የሚፈጸም ድርጊት ነው። በዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የሳይበር ጥቃት የሚያካትተው፤ ስለ አንድ ሰው የግል ገመና ወይም የግል መረጃዎችን መጥለፍ፣ ማሠራጨት፣ መለጠፍ፣ ወይም ለሌሎች ማጋራት ሲሆን ይህም አሳፋሪ ወይም የማዋረድ አንደምታ የሚያስከትል ነው። ይህ ድርጊት የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎችን፣ ክሮም ቡኮችን፣ ላፕቶፖችን፣ እና ዲፕ ፌክ የመሳሰሉ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መጠቀምን ያካትታል፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የሳይበር ጥቃት በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ቢከሰት፣ ባህሪው በቀጥታ የትምህርት ቤት ደህንነትን እና ስራዎችን የሚጎዳ ከሆነ ድርጊቱን በፈጸሙት ተማሪዎች ላይ ተመሳሳይ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ንብረት ላይ በማንኛውም መልክ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን፣ ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን ፣እና ማስፈራራትን ይከለክላል (የቦርድ ፖሊሲ JHF)።

ተማሪዎች በትምሕርት ቀን የግል የሞባይል መሳሪያዎችን መጠቀም ይችላሉ?

አይችሉም፡- ደንብ COG-RA፣ የግል ሞባይል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ በትም ሕርት ቀን የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ተማሪዎች የግል ሞባይል መሳሪያዎችን እንዳይጠቀሙ ይከለክላል።

የትምህርት ቀን ማለት፡- በትምህርት ቀን ላይ የመጀመሪያው ደወል ሲደወል ጀምሮ እስከ ትምህርት ቀን መጨረሻ የሚለቀቁበት የመጨረሻ ደወል እስከሚደወል ድረስ የሚከናወን ማንኛውም የተዋቀረ ወይም ያልተዋቀረ የትምህርት ተግባር ማለት ሲሆን ይህም የትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን፣ የምሳ ሰአቶችን፣ የእረፍት ጊዜዎችን፣ ከአንድ የመማሪያ ክፍል ወደ ሌላ የመማሪያ ክፍል የሚተላለፉባቸው ጊዜዎችን እና የሽግግር ጊዜዎችን ያጠቃልላል።

የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያ (PMD) ከኢንተርኔት ጋር ለመገናኘት እና በድምጽ፣ በቪዲዮ፣ ወይም በጽሑፍ ውሂብ ለመላክ ወይም ለመቀበል የሚያገለግል ማንኛ ውንም ከ MCPS ያልተሰጠ መሳሪያን ያመለክታል። ሞባይል ስልኮች፣ e-readers፣ ታብሌቶች፣ ክሮምቡክ፣ የግል ኮምፒውተሮች፣ ስማርት ሰዓቶች፣ ስማርት መነጽሮች፣ ወይም ማይክሮፎኖች፣ የጆሮ ማዳመጫዎች (ኤርፖድስ፣ የጆሮ ማዳመጫዎችን ጨምሮ)፣ ድምጽ ማጉያዎች እና/ወይም ካሜራዎች የተገጠሙ ሌሎች መሳሪያዎች ሁሉም PMDዎች እንደሆኑ ይቆጠራሉ። ሆኖም፣ ተማሪዎች MCPS ንብረት እና MCPS ስፖንሰር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ PMD ሊኖራቸው ይችላል።

ይህንን ደንብ የሚጥስ ማንኛውም ተማሪ MCPS የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል። MCPS ለአንድ የኤሌክትሮኒክስ መሳርያ መጥፋት፣ መሰረቅ፣ ወይም መበላሸት ወይም ያለፈቃድ PMD አጠቃቀም ሃላፊነት ወይም ተጠያቂነት የለበትም።

(ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት COG-RA፣ የግል ሞባይል መሳሪያዎች፣ ILA-RA፣ ከደህንነት እና ከሪፖርት ማድረግ መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ ግምገማዎችን እና IGT-RA፣ ስለ ኮምፒውተር ስርዓቶች፣ ስለ ኤሌክትሮኒክስ መረጃ እና ስለ ኔትወርክ ደህንነት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች ድንብይመልከቱ።)

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፐሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፐሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ከክፍል ማቋረጥ** (101) | ወደ ትምህርት ቤት ከደረሱ በኋላ ያለምክንያት ክፍል ውስጥ አለመገኘት።[1] | | | | | | ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብቻ<br>የሜሪላንድ የትምህርት ኮድ 7-305 ተማሪዎች በትምህርት ሰዓት ክፍል ውስጥ ባለመገኘታቸው ምክንያት ብቻ ከትምህርት ቤት እንዲታገዱ አይፈቅድም። ከፍተኛ ደረጃ የዲሲፐሊን እርምጃ የሚወሰደው (በትምህርት ቤት ውስጥ ከክፍል ማገድ) ትምሕርት ካለመከታተል ባሀሪ ያለፈ ጥፋት መሆን አለበት። |
| | | ት/ቤት ከደረሱ በኋላ የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር በተከታታይ ከክፍል መቅረት።[1,2]<br>የሜሪላንድ የትምህርት ኮድ §7-305 ተማሪዎች በትምህርት ሰዓት ክፍል ገብተው ባለመከታተላቸው ምክንያት ብቻ ከትምሕርት እንዲታገዱ ወይም እንዲባረሩ አይፈቅድም። | | | | | |
| **ማርፈድ** (102)<br>MCPS ደንብ JEA-RA፣ ስለ ተማሪ የትምሕርት ክትትል ይመልከቱ፡- | የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር ወደ ክፍል ወይም ወደ ት/ቤት ከአንድ ጊዜ በላይ ዘግይቶ መድረስ።[1,2] | | | | | | ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ብቻ<br>የሚያረፍዱ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የከበደ ቅጣት ወይም የማግለል እርምጃ መሰጠት የለባቸውም፣ ነገር ግን ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው እንዲያውቁት መደረግ አለበት። |
| | | ዘወትር ያለበቂ ምክንያት ወደ ክፍል ወይም ትምህርት ቤት ዘግይቶ መምጣት።[1,2] | | | | | |
| **ውስልትና/ዋልጌነት** (103)<br>MCPS ደንብ JEA-RA፣ ስለ ተማሪ የትምህርት ክትትል ይመልከቱ | ባልተፈቀደ ምክንያት ከት/ቤት መቅረት።[1,2] | | | | | | በህጋዊም ሆነ በህገ-ወጥ መንገድ ከመጠን በላይ አዘውትሮ መቅረት እና/ወይም ዘግይቶ መምጣት የሚያዘወትሩ ተማሪዎች ወደ ተማሪዎች ደህንነት ቡድን (SWBT) ሊላኩ ይችላሉ። SWBTs ለተደጋጋሚ መቅረት ዋና መንስኤ እና መደበኛ የትምህርት ክትትልን ለማጎልበት የተነደፉ ተገቢ የጣልቃገብነት እርምጃዎችን የመወሰን ሂደት ይተገብራል። በተደጋጋሚ መቅረት ስለሚያበዙ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን የትምህርት ቤት ክትትል ሁኔታ በተመለከተ እንዲያውቁ ይደረጋ። |
| | | ውስልትና/ዋልጌነት[3] | | | | | |
| | | | ያለ ፈቃድ ከት/ቤት ግቢ/ካምፓስ ለቆ መውጣት። | | | | |

[1] አንድ ተማሪ "ት/ቤት አለመገኘት ጋር በተያያዙ ጉድለቶች ምክንያት ብቻ" ከት/ቤት ሊታገድ ወይም ከት/ቤት ሊሰናበት አይችልም። MD ANN CODE, EDUCATION § 7-305. ይህ በዚህ ገፅ በተዘረዘሩት ሁሉም ስነምግባሮች ላይ፡- ከክፍል መቅረት፣ መዘግየት፣ እና ዋልጌነት ተግባራዊ ይሆናል።

[2] የመቅረት ፈቃድ የሚያሰጡ ምክንያቶች፡- ቤተሰብ ውስጥ የሚያጋጥም ሞት፣ የተማሪዋ(ው) ወይም የተማሪዋ(ው) ልጅ ህመም፣ እርግዝና፣ እና ከወላጅነት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች፣ የፍርድ ቤት ቀጠሮ፣ አደገኛ የአየር ሁኔታዎች፣ ሃይማኖታዊ በዓልን ለማክበር፣ የስቴቱ ድንገተኛ ሁኔታ፣እገዳ፣ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር ያደረገው እንቅስቃሴ፣ እና MCPS ደንብ JEA-RA፣ የተማሪዎች በትምህርት ላይ ስለመገኘት ደንብ ላይ የተገለጹ ሌሎች ሁኔታዎች፣COMAR። 13A.08.01.03.

[3] አንድ ተማሪ በማንኛውም ሩብ አመት ከ 8 ቀኖች በላይ፣ በአንድ ሴሚስተር 15 ቀኖች፣ ወይም በትምህርት አመት ውስጥ 20 ቀኖች "ከትምህርት ቤት ሳያስፈቅድ መቅረት" (በግምት 10%) ያለፈቃድ መቅረት ነው። MD ANN CODE, EDUCATION § 7-355.

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1 መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2 በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4 በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5 በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6 በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **አልኮሆል (201)**<br>የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ MCPS ውስጥ አልኮሆል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን አላግባብ መጠቀምን ስለመከላከል፣ የሞንትጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች፦ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌላ<br>MCPS ንብረት ውስጥ አደንዛዥ መድሃኒቶችን ስለመጠቀም፣ እና IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚያካትት የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ክስተቶችን የሚመለከቱ መመሪያዎች | | | አልኮል ጠጥቶ መግባት፣ አልኮል መጠቀም፣ ወይም የአልኮል መጠጥ ይዞ መገኘት።[6,8] | | | | እንደ ማንኛውም የዲሲፐሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ወይም MCPS የመከላከል እና የህክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት። |
| | | | | አልኮልን ለሌሎች ማሰራጨት/መሸጥ።[7] | | | |
| **በትንፋሽ በመሣብ የሚወሰዱ እፆች/ INHALANTS (202)[8]**<br>የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ MCPS ውስጥ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀምን ስለ መከላከል፦ MCPS ደንቦች፡ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌላ<br>MCPS ንብረት ውስጥ መድሃኒቶችን፣ እና IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚያካትት የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ክስተቶችን የሚመለከቱ መመሪያዎች | | | በትንፋሽ የሚሳቡ እፆችን መውሰድ፣ መጠቀም፣ ወይም ይዞ መገኘት[6,8] | | | | እንደ ማንኛውም የዲሲፐሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ክፍል ወይም MCPS የመከላከል እና የህክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት። |
| | | | | በትንፋሽ እየሳቡ የሚጨሱ እፆችን ማሰራጨት/መሸጥ[7,9] | | | |

[6]ተማሪው(ዋ) በአልኮል፣ በአደንዛዥ እፅ ወይም በሌሎች አደንዛዥ ንጥረ ነገሮች ተጽዕኖ ስር ከተገኘ(ች) እና በትምህርት ቤቱ የጤና አገልግሎት ከሌለ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ቤት መላክ እና ተማሪው(ዋ)ን ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ወይም ወደ ማህበረሰብ የጤና ተቋም ማስተላለፍ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ተማሪው(ዋ)ን ወደ ቤት ከመላክ በፊት፣ተማሪው(ዋ) የት/ቤቱን ግቢ ሲለቅ/ስትለቅ በአንድ የቤተሰብ አባል ወይም ለመርዳት በሚችል ግለሰብ መታጀቡን/መታጀቧን ለማረጋገጥ ት/ቤቱ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል። MCPS ፖሊሲ IGN በሞንጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ት/ቤቶች ውስጥ የአልኮል፣ የትምባሆ፣ እና የሌሎች ጎጂ መድሃኒቶችን ህገ-ወጥ አጠቃቀምን መከላከል በተጨማሪ ይመለከቱ።

[7]የት/ቤት ስነስርአት የማስከበር ጉዳይን በሚመለከት፣ አልኮል፣ በትንፋሽ እየተሳበ የሚጨሱ መድሀኒቶች/የተከለከሉ እፆችን ስርጭት፣ ሽያጭ ወይም የመሸጥ አዝማምያ መከላከል።

[8]ለመረጃ ያክል፣ የአካል ጉዳተኝነት ላላቸው ተማሪዎች ብቻ፡ በኮድ 892 ተጠቀሙ። (ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች "የህገወጥ እፆች" ትርጉም በህጋዊ መንገድ ያልተገኙ ነገሮች፣ ህጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ቁጥጥር ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል፣ ወይም ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው መዳኒቶች አጠቃቀም ደንብ ወይም በሌላ የፌደራል ህግ እውቅና በተሰጠው ባለስልጣን ቁጥጥር አገልግሎት ላይ የሚውል ማለት ነው።)

[9]ለመረጃ አያያዝ እንዲያመች፣ የአካል ጉዳት ላላቸው ልጆች ብቻ፣ 21 U.S.C. § 812; 21 C.F.R. pt. 1308 ቁጥጥር የሚደረግባቸው መዳኒቶች ዝርዝሮች ውስጥ የተለዩ እፆችን ስለመሸጥ በኮድ ቁጥር 891 ይጠቀሙ።

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **አደንዛዥ ዕፅ ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች** (203)[10]<br>የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ MCPS ውስጥ አልኮሆል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች አደንዛዥ እፆችን አላግባብ መጠቀምን ስለመከላከል፦ MCPS ደንቦች፦ COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ፣ COFRA፣ አልኮሆል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች MCPS ንብረት ላይ አደንዛዥ መድሃኒቶችን መውሰድ፣ እና IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ክስተቶችን የሚመለከቱ መመሪያዎች፣ JPC-RA፣ ለተማሪዎች መድሃኒት አስጣጥ<br>*በሀኪም ያልታዘዙ ጉዳት የሚያስከትሉ ንጥረነገሮች ለጎጂ ዓላማዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ እና በሀኪም የታዘዘ ለተማሪ የሚሰጥ መድኃኒት እና ከ 21 አመት በታች የሆኑ ግለሰቦች በሜሪላንድ ውስጥ በህጋዊ መንገድ ሊጠቀሙባቸው ስለማይችሉ ምርቶች IGO-RA መመሪያዎችን ይመልከቱ። | | JPC-RA፣ ለተማሪዎች ስለ መድሀኒት አሰጣጥ ደንብ በመጣስ "ራስን መርፌ መውጋት" በሀኪም ያልታዘዘ መድሃኒት መውሰድ። | | | | | |
| | | | Regulation JPC-RA. ደንብን በመጣስ የትምሕርት ቤት የጤና ባለሙያ ነርስ ፈቃድ ሳይሰጥ (መድኃኒት የታዘዘለ(ላ)ት ተጠቃሚ) "መድሃኒት ይዞ መገኘት"። | | | | |
| | | | | ደንብ JPC-RA ወይም ደንብ IGO-RA በመጣስ መድሃኒት መጠቀም፣ ይዞ መገኘት፣ ወይም በመድኃኒት ተጽእኖ ስር መሆን። | | | |
| | | | | ደንብ JPC-RA. በመጣስ ያለ ሀኪም ትእዛዝ ከፋርማሲ መደርደርያ የሚገዙ መድኃኒቶችን ለሌሎች ተማሪዎች ማጋራት፣ መሸጥ፣ መያዝ ወይም መጠቀም። | | | |
| | | | | ደንብ JPC-RA. በመጣስ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን ለሌሎች ተማሪዎች ማጋራት፣ መሸጥ፣ መያዝ ወይም መጠቀም። | | | እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም ወደ MCPS የበሽታ መከላከያ እና ሕክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት።<br>ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ፣ የሚመለከተው ሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለክስተቱ ምላሽ ለመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል። |
| | | | | | እንደ ካናቢኖይድስ የመሳሰሉ ከ 21 ዓመት እድሜ በታች ለሆኑ ግለሰቦች መጠቀም በሕጋዊነት የማይፈቀድላቸው ነገር ግን በሜሪላንድ ስቴት ሕጋዊ የሆኑ አደንዛዥ እፆችን/መድኃኒቶችን ወይም ንጥረ ነገሮችን ለሌሎች ተማሪዎች ማጋራት፣ መሸጥ፣ መያዝ ወይም መጠቀም።[11]<br>(በምንም አይነት ሁኔታ ተማሪዎች ካናቢስ ወይም ካናቢኖይድስ ለህክምና አገልግሎትም ሆነ ለሌላ በራሳቸው መውሰድ አይፈቀድላቸውም) | | |

[11] የሚያሰጋ ባህሪ ምርመራዎች የት/ቤቱን የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ አስፈላጊነት መገደብ የለባቸውም።

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ትምባሆ (204)**<br>የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ MCPS ውስጥ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ መጠቀምን ስለመከላከል፣ MCPS ደንቦች፣ COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ፣ COFRA፣ አልኮሆል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች MCPS ንብረት ላይ የሚወሰዱ መድሃኒቶች፣ እና IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ክስተቶችን የሚመለከቱ መመሪያዎች፣ JPC-RA፣ ለተማሪዎች ስለ መድሃኒት አሰጣጥ መመሪያ<br>ካናቢኖይድስ «ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች/ መድሃኒቶች (203) ስር ይመደባል። | | | IGO-RA ሲጋር፣ ሲጃራ፣ ጋያ፣ ወይም ሌላ የትምባሆ ምርት እና ማንኛውንም የሚጨስ ነገር መጠቀም፣ መያዝ፣ ወይም ማከፋፈል የተከለከለ ነው። ይህ ከማጨስ ጋር የሚገናኝ ማንኛውንም አይነት ነገሮችን ያካትታል።<br>(በምንም አይነት ሁኔታ ተማሪዎች ካናቢስን ለህክምና አገልግሎት ወይም ለሌላ ምክንያት እንዲወስዱ አይፈቀድላቸውም) | | | | እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ክፍል ወይም ወደ MCPS የበሽታ መከላከያ እና ህክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት። |
| **የጦር መሳሪያዎች (301)** | | | | | | ተተኳሽ መሣሪያ መያዝ (ለምሳሌ፦ ሽጉጥ)[11] | ክስተቱ ወዲያውኑ ለሚመለከተው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ እንዲሁም ለትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ሪፖርት መደረግ አለበት። የሚመለከተው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለተፈጠረው ክስተት ምላሽ በመስጠትና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ይኖረዋል። ደንብ COB-RA ስለ ክስተት ሪፖርት ማድረግይመልከቱ። |

[11]በፌደራል እና በሜሪላንድ ስቴት ህግ መሰረት የጦር መሳርያ ይዞ/ዛ ወደ ት/ቤት የመጣ/ች ተማሪ "ቢያንስ ለ1 አመት ከት/ቤት ይወገዳል/ትወገዳለች፣ ነገር ግን አንድ የካውንቲ የበላይ ተቆጣጣሪ "የካውንቲው ቦርድ የትምህርት አማራጮችን ካፀደቀ፣ እያንዳንዱን ጉዳይ በየቅል እየለየ፣ አጠር ያለ የማሰናበቻ ጊዜ ወይም የትምህርት አማራጭ ሊወሰን ይችላል።" MD ANN CODE, EDUCATION § 7-305(f)(2)-(3); COMAR 13A.08.01.12-1። ሆኖም ግን፣ ሽጉጥ ወይም ተተኳሽ መሣሪያ ይዞ ወደ ትምህርት ቤት የመጣ(ች) የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ቅጣት፣ ከትምህርት ቤት እገዳ፣ ከትምህርት ቤት መባረርን ወይም ጊዜያዊ አማራጭ ምደባን ጨምሮ፣ IDEA MD ANN CODE፣ EDUCATION § 7-305(g) መስፈርቶች መሠረት መከናወን አለበት፣ COMAR 13A.08.01.12-1(C)። ለመረጃ አያያዝ አንዲያመች፣ የአካል ጉዳተኝነት ላላቸው ተማሪዎች ኮድ 893 ይመለከቷል።

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1 መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2 በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4 በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማገለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5 በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማገለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6 በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማገለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ሌሎች የጦር መሣሪያ ጠመንጃዎች (302)**<br>*MCPS ደንብ COE-RA፣ ስለ ተተኳሽ መሳርያዎችይመልከቱ። | | | የጦር መሳሪያ የሚመስል ፋሲሚል (ለምሳሌ፦ የአሻንጉሊት ሽጉጥ፣ የውሃ ሽጉጥ፣ ወይም ሌላ የሚመሳሰል ሽጉጥ) መያዝ | | | | "ብራንዲሽ/Brandish" ማለት በቁጣ ወይም በጨዋታ መልክ መሳሪያውን በሚያስጋ ሁኔታ ማወዛወዝ/ማሽከርከር ወይም መደቀን ማለት ነው። |
| | | | | (BB, pellet, cap, gel blaster, ወይም airsoft gun) እና ሌላ በማስመሰል የተሠራ ሽጉጥ (brandishing ሳያደርጉ ወይም ሳያስፈራሩበት) ለመጠቀም መያዝ። | | | |
| | | | | (BB፣ pellet፣ cap፣ gel blaster፣ ወይም airsoft gun) በማመሳሰል የተሠራ ሽጉጥ መያዝ፣ ማሳየት፣ መጠቀም ወይም ማስፈራራት | | | |
| **ቢላዋ፣ ጩቤ፣ ሴንጢ፣ እና ሌሎች ጎጂ መሳርያዎች (303)**<br>*MCPS ደንብ COE-RA፣ የጦር መሳርያዎችይመልከቱ። | | | | እንደ መሳሪያ ለመጠቀም በመነሳሳት ከባድ የአካል ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ቢላዋ ወይም ሌላ መሳሪያ ይዞ መገኘት። | | | "ብራንዲሽ/Brandish" ማለት በቁጣ ወይም በጨዋታ መልክ መሳሪያውን በሚያስጋ ሁኔታ ማወዛወዝ/ማሽከርከር ወይም ሰው ላይ መደገን ማለት ነው። |
| | | | | | ከባድ የአካል ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ቢላዋ ወይም ሌላ ጎጂ መሳሪያን መደገን፣ መቃጣት፣ መጠቀም ወይም መሣሪያ ይዞ ማስፈራራት። | | |
| **በጎልማሳ ሰው ላይ ጥቃት ማድረስ(401)**<br>MCPS ደንብ COB-RA፣የአደጋ ክስተቶችን ሪፖርት ስለማድረግ | | | | | የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ሰራተኛ ወይም ሌላ አዋቂ ሰውን በአካል ማጥቃት፣ ሆን ብሎ መግፋት፣ ወይም በሌላ መልኩ አካላዊ ጥቃት ማድረስን ጨምሮ፤ በድብድብ ውስጥ መሳተፍ፣ ወይም ግጭትን ወይም ሌላ የረብሻ ክስተትን ለመከላከል ወይም ለማስታገስ ጣልቃ የሚገባ ሰራተኛን ሆን ብሎ መምታት።<br>አንድን ተማሪ IEP ወይም 504 ድንጋጌ መሠረት የቅጣት እርምጃ ከመውሰድ አስቀድሞ፣ የሚያስከትሉትን ውጤቶች ከእነዚህ እቅዶች ጋር ማገናዘብ ይጠበቅብዎታል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ መገለጫ የመስጠት ወይም የተፈጠረውን ሁኔታና ምክንያቱን ለመገምገም ስብሰባ ሊያስፈልግ ይችላል። | | ተማሪው(ዋ) የባህሪ ጤና መቃወስን ሊጠቁም የሚችል ሁኔታ ሲታይበ(ባ) ት መምህሩን እና ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች ችግሩን ለመፍታት ደንብ IOH-RA ላይ እንደተገለጸውተማሪዎች የባህሪ ጤና አገልግሎት ወደሚያገኙበት ማስተላለፍወደሚመለከተው ብቁ እና የሰለጠነ ቡድን ማስተላለፍ እና ለተማሪው(ዋ) ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኝ/እንድታገኝ ማድረግ አለባቸው።<br>ቀደም ሲል ለተከሰተ ተመሳሳይ ባህሪ ወይም ፖሊሲ ACA እና ደንብ JFA-RA ውስጥ ለተገለጹ ሁኔታዎች ወይም ምልክቶች የባህሪ ማስተካከል ጣልቃ ገብነት እርምጃ አወሳሰድ ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል።<br>ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ፣ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ፣ የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለክስተቱ ምላሽ በመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል። |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1 መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2 በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4 በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5 በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6 በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **በተማሪ ላይ የሚፈፀም ጥቃት (402)**<br>MCPS ደንብ COB-RA፣የአደጋ ክስተትን ሪፖርት ስለማድረግ | | | | የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) ተማሪ ላይ አካላዊ ጥቃት ማድረስ፣ ሆን ብሎ መግፋት፣ መገፍተር፣ ወይም በሌላ መልኩ አካላዊ ጥቃት መፈፀምን ጨምሮ (ለምሳሌ፦ ሰውነትን መበርበር/መፈተሽ፣ ሆን ብሎ መጋጨት፣ መራገጥ)። | | | ትምህርት ቤቶች የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፦<br>• ተማሪው(ዋ) አስቀድሞ(ማ) ያሰበ(ች)ው/ያቀደ(ች)ው ሳይሆን በወቅቱ ባጋጠመ ድንገተኛ ሁኔታ ተነሳስቶ(ታ) ፈፅመ(ች)ው እንደሆነ<br>• ተማሪው(ዋ) ሌሎችን ለመደብደብ የሚያነሳሳ የማናደድና የማስቆጣት ተግባር ፈፅሞ(ማ) እንደሆነ<br>• ተማሪው(ዋ) ራስን ለመከላከል አድርጎት/አድርጋዉ እንደሆነ<br>ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ፣ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ፣ የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለክስተቱ ምላሽ በመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል። |
| | | | | | በተዘረዘሩት ምክንያቶች በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) ተማሪ ላይ የአካል ጥቃት መፈፀም፣ እጅና እግር መስበር፣ ወይም በሌላ መልኩ ከባድ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ጥቃት ማድረስ። | | |
| **በጎልማሳ ሰው ላይ የሚደረግ ዛቻ (403) በተማሪ ላይ የሚደረግ ዛቻ (404)**<br>የቦርድ ፖሊሲ COA፣ MCPS ደንብ COA-RA | | | የሚያስጋ ማስፈራርያ ቋንቋ እና/ወይም ምስሎችን መጠቀም (የቃል፣ የጽሑፍ፣ የዲጂታል/ኤሌክትሮኒክስ፣ በስውር ወይም በግልጽ የዛቻ ቋንቋን መጠቀም) በሰራተኛ ላይ፣ በተማሪ ላይ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰው ላይ በአካል የሚደረጉ የዛቻና የማስፈራራት ምልክቶችን መጠቀም። | | | | ከዲሲፕሊን እርምጃ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች የባህሪ ስጋት ግምገማ ማካሄድ አለባቸው። |
| **ድብድብ (405)**<br>*የቦርድ ፖሊሲ JHF፦ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት እና MCPS ደንብ JHF-RA የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት እና MCPS ቅጽ 230-35 ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራትን ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ይመልከቱ።<br>** MCPS ደንብ JHG-RA፣ ወንበዴዎች፣ የወሮበሎች እንቅስቃሴ፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አጥፊ ወይም ህገወጥ ቡድንን ባህሪ መከላከል MCPS ቅጽ 230-37፣ ከወሮበላ ቡድን ጋር የሚገናኝ ክስተት ሪፖርት ማድረግያ ቅጽ | | | መጠነኛ ቁስል ያስከተለ ድብድብ ውስጥ መሳተፍ። | | | | ት/ቤቶች የሚከተሉትን ጨምሮ በርካታ ሁኔታዎችን ማገናዘብ አለባቸው፦<br>• ተማሪው(ዋ) አስቀድሞ(ማ) ያሰበ(ች)በ(ት/ያቀደ(ች)ው ሳይሆን በወቅቱ ባጋጠመ ድንገተኛ ሁኔታ ፈፅሞት/ፈጽማዉ እንደሆነ<br>• ተማሪው(ዋ) የተናደደ(ች) እና እራስን ለመከላከል ያደረገ(ች)ው እንደሆነ ወይም ተማሪው(ዋ) ሌሎችን እንዲደባደቡ ያነሳሳ ከሆነ<br>• ተማሪው(ዋ) ረብሻን ለማርገብ ምክንያታዊ እርምጃዎችን የወሰደ(ች) ወይም ተማሪዎችን ለመገላገል ባደረገ(ች)ው ጣልቃ መግባት ምክንያት ከሆነ |
| | | | | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | |
| | | | | | በተጠቀሱት ምክንያቶች የትምህርት ቤት ሰራዎችን የሚያደናቅፍ እና/ወይም እጅና እግር ወይም ሌሎች ከባድ የአካል ጉዳቶችን የሚያስከትል ረብሻ በመፍጠር በግል ወይም በቡድን ጠብ ውስጥ መግባት/መሣተፍ። | | |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **በኃይል ማስገደድ/ዛቻና ማስፈራራት (406)**<br>MCPS ደንብ COB-RA | | | | አንድ ሰው ንብረቱን እንዲሰጥ በዛቻ፣ በማስፈራራት፣ ወይም በሃይል (ያለጠብመንጃ ወይም ያለሽጉጥ) ማስገደድ። | | | ከዲሲፕሊን እርምጃ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች የባህሪ ስጋት ግምገማ ማካሄድ አለባቸው። |
| | | | | | በዛቻ፣ በማስፈራራት፣ በሃይል፣ ወይም መሳርያ በመጠቀም) አንድ ሰው ንብረቱን እንዲያስረክብ ማስገደድ። | | |
| **ማሸማቀቅ/ማዋከብ**<br>የቦርድ ፖሊሲ ACF፣ JHF፣ MCPS ደንቦች ACF-RA፣ ACI-RA፣ COB-RA፣ JHF-RA | | | ጉልበተኝነት—በመመሪያ JHF ውስጥ የተከለከሉ የስነምግባር መስፈርቶችን በሚያሟሉ ተማሪዎች ያልተፈለገ፣ ወራዳ ባህሪ ውስጥ መሳተፍ/ማነሳሳት።<br>የሳይበር ጥቃት—ግለሰቦች ዲጅታል ይዘቶችን እንዲመለከቱ ወይም እንዲያጋሩ በማድረግ የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት የሚተላለፍ ጥቃት መፈፀም። የሳይበር ጥቃት በአንድ ሰው ላይ ሃፍረትን ወይም ውርደትን እንዲያስከትል ለማድረግ ግላዊ ማንነት ወይም የግል መረጃን ለሌሎች ማስተላለፍን፣ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ላይ መለጠፍ ወይም ማጋራትን ያካትታል። ይህ የግል ተንቀሳቃሽ ሞባይል ስልኮችን እና የውሸት መረጃዎችን መፈብረክ የመሳሰሉ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መጠቀምን ያካትታል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም።<br>ትንኮሳ—የአንድን ግለሰብ ትክክለኛ ወይም የሚገመት የግል ባህሪን ተሞርኩዞ ሌላ ግለሰብን የሚያስከፋ፣ የማፌዝ ወይም የሚያዋርድ አሉታዊ ድርጊት ውስጥ መሳተፍ/ማነሳሳት። ጾታዊ ብልግናን የሚያካትት ወሲባዊ ድርጊትን፣ ወሲባዊ ጥቃትን፣ እና ወሲባዊ ትንኮሳን ያጠቃልላል። | | | | እንደማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካ፣ ት/ቤቶች የባህርይ ማስተካከያ ስልቶች ላይ ማተኮር እና ተማሪዎችን ተገቢ ካውንስሊንግ ወደሚያገኙበት ማስተላለፍ አለባቸው።<br>የተማሪው(ዋ) ድርጊት፣ በተጎጂው ዘር፣ ቀለም፣ ብሔር፣ ሃይማኖታዊ እምነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ ቤት አልባነት ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት የተፈፀመ ከሆነ፣ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሪፖርት መደረግ አለበት።<br>የሳይበር ጥቃት ግለሰቦችን ኢላማ በማድረግ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን፣ የማህበራዊ ሚዲያዎችን፣ ወይም አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን መጠቀምን ያጠቃልላል። ይህ በግልጽ ዲጂታል ማመሳሰልን፣ ያልተፈቀደ ወይም የሀሰትና የተጭበረበረ የማህበራዊ ሚዲያ መገለጫዎችን መፍጠር፣ እና ስለ ሌሎች ግለሰቦች ለመግለጽ፣ ለማታለል፣ ወይም ለማዋረድ የድምፅ ቀረጻ ቴክኖሎጂን ወይም የፈጠራ የድምጽ ሲስተሞችን መጠቀምን ያካትታል።<br>ስለ ጾታዊ ብልግና ወይም ስለ ጾታዊ ትንኮሳ ክስተቶች፣ አስተዳዳሩ ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የተማሪዎች ሥነ ምግባር እና አቤቱታ ክፍል ሰራተኞችን ማማከር አለበት። |
| | | | | ማስፈራራት—በሌላ ግለሰብ ላይ የፍርሃት ወይም የበታችነት ስሜትን በመሰነዘር የሚያስፈራራ ወይም የሚያነሳሳ ድርጊት ውስጥ መሳተፍ/ማነሳሳት። ለብቀላ ዛቻ ማድረግ እንደ ማስፈራሪያ ሊቆጠር ይችላል። | | | |
| | | | ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያበረታታ ቋንቋን መጠቀም ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን መንዛት በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል። | | | | |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| ከባድ የአካል ጉዳት (408) | | | | ሳይታሰብ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ህለና መሣትን በሚያስከትል ድርጊት ላይ መሳተፍ። | | | ከባድ የአካል ጉዳት ማለት (ከባድ የአካል መጎዳት) ሰፊ የሕክምና እርዳታ ወይም የሆስፒታል ህክምና የሚያስፈልግ በውጫዊ አካል ወይም ኃይል በሰውነት አካል ወይም እንቅስቃሴ ላይ የሚደርስ ከባድ የአካል ጉዳት ነው። እንደዚህ አይነት አካላዊ ጉዳቶች ከፍተኛ የሞት አደጋን፣ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ የሆነ የአካል ክፍልን ማሰናከል፣ የአካል ክፍል መጉደል ወይም የአእምሮ ጉዳት፣ ወይም ጥቅም ማጣት፣ ራስን መሳት፣ የአካል መበላሸት እና/ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የአካል ህመምን የሚያካትቱ ናቸው። |
| | | | | | ሆን ተብሎ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም የህለና መሣት በሚያስከትል ድርጊት ላይ መሳተፍ። | | |
| ንብረት ማውደም/ ማቃጠል (501) | | | | ሌሎችን አደጋ ላይ ለመጣል ሳታስብ እሳት መለኮስ ወይም እሳት እንዲለኩሱ ሌሎችን መርዳት። | | | ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ፣ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ፣ የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለክስተቱ ምላሽ በመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል። |
| | | | | | ሌሎችን አደጋ ላይ ለመጣል ወይም ንብረትን ለማውደም በማሰብ በእሳት ማቃጠል ወይም እሳት እንዲለኩሱ መርዳት። | | |
| በውሸት የሚደረግ የአደጋ ጥሪ ወይም የማስጠንቀቂያ ደወል (502) | | | | በስልክ፣ PMD ወይም በአካል (ለምሳሌ:- የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል መደወል፣ 911 አካባቢብ መጥራት) ስለ እሳት አደጋ ወይም ሌላ ጥፋት ማስፈራራት፣ ያለ ምክንያት የእሳት ማጥፊያን ማበላሸት ወይም መንቀል። | | | ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ፣ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ፣ የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለክስተቱ ምላሽ በመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል። |
| በቦምብ ዛቻ ማድረግ(502)<br>ክስተትን ሪፖርት ስለማድረግ MCPS ደንብ COB-RA ይመልከቱ | | | | የቦምብ ዛቻ ማድረግ ወይም በት/ቤት ተኩስ ለመክፈት ማስፈራራት። ማስፈራራት/ዛቻ በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምስሎች፣ በኦንላይን እና/ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ምንጮች አማካኝነት ያልተፈቀደ ወይም ሀሰተኛ የመረጃ ስርጭት ማድረግን ያካትታል፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። | | | ከዲሲፕሊን እርምጃ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች የባህሪ ስጋት ግምገማ ማካሄድ አለባቸው።<br>ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ፣ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ፣ የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለክስተቱ ምላሽ በመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል። |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1 መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2 በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4 በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5 በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6 በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ አገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ፈንጂ (503)** *MCPS ደንብ COB-RA፣የአደጋ ክስተት ሪፖርት ስለማድረግ ይመልከቱ | | | | በሰው እና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ የሚችሉ፣ ከጠመንጃ ሌላ፣ የሚፈነዳ መሳርያ፣ ወይም የሚቃጠልና የሚፈነዳ ነገር መያዝ (ለምሳሌ፦ ርችት፣ የጢስ ቦምብ፣ ብልጭታ ያላቸው ነገሮችን፤ነገር ግን "snap pops" አያካትትም)። | | | |
| | | | | ከላይ እንደተገለጸው፣ፈንጂ ወይም የሚፈነዳ መሳርያ መያዝ ወይም ማፈንዳት ወይም ለማፈንዳት ማስፈራራት። | | | |
| ***ወሲባዊ ጥቃት (601)** *የተማሪ ስነምግባር ደንብ/ኮድ እና ይግባኝ ሰሚ ክፍል ማነጋገርን የመሳሰሉ MCPS የሪፖርት አቀራረብ ፕሮቶኮሎችን ይከተሉ። | | | | በአካል በማስገደድ ጾታዊ ተግባር ላይ መሳተፍ። | | | እንደማንኛውም የስነስርአት ርምጃ፣ የት/ቤት ሰራተኞች ተማሪዎችን ወደሚመለከተው የምክር አገልግሎት ማስተላለፍ አለባቸው።<br>አስገድዶ መድፈር እና/ወይም ያለስምምነት የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ በአስቸኳይ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። ደንብ COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ |
| ***ፆታዊ ጥቃት (602)** የቦርድ ፖሊሲ ACF፣ JHF፣ MCPS ደንቦች ACF-RA፣ ACI-RA፣ COB-RA | | | | ያልተፈለገ የወሲብ ጥቃት መፈፀም፣ ፆታዊ ጥቅም መጠየቅ እና/ወይም ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ የቃል፣ የጽሑፍ፣ የዲጂታል፣ የኤሌክትሮኒክስ ወይም አካላዊ ንክኪዎችን ማድረግ። | | | እንደማንኛውም የስነስርአት ርምጃ፣ የት/ቤት ሰራተኞች ተማሪዎችን ወደሚመለከተው የምክር አገልግሎት ማስተላለፍ አለባቸው።<br>ከታይትል IX አስተባባሪ ጋር በመመካከር፣ ት/ቤቶች እድሜን፣ የክፍል ደረጃን፣ የእድገት ደረጃን፣ ቀድሞ የተፈጸሙ ጥፋቶችን፣ ሆን ተብሎ የሚፈጸሙ ጥፋቶችን እና ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ህጋዊ በሆነ መንገድ ምላሽ ይሰጣሉ። |
| **ወሲባዊ ተግባር (603)** | | | ተገቢ ያልሆነ ወሲብ ቀስቃሽ ባህርይ (ለምሳሌ፦ በት/ቤት ንብረት ውስጥ የሰውነት መጋለጥ፣ ወሲባዊ ጽሑፎችን መላላክ፣ ወሲባዊ ድርጊቶችን መፈፀም)። | | | | እንደማንኛውም የስነስርአት እርምጃ፣ የት/ቤት ሰራተኞች ተማሪዎችን ወደሚመለከተው የምክር አገልግሎት መምራት አለባቸው።<br>አስገድዶ መድፈር እና/ወይም ስምምነት የሌላቸው ወሲባዊ ድርጊቶች ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ በአስቸኳይ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። ደንብ COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1 መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2 በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4 በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5 በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6 በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ንቀት፣ አለማክበር** (701)<br>*አለመታዘዝ ከንቀት፣ አለማክበር ጋር ተጠቃልሏል። | ተገቢ ያልሆኑ ወይም ጎጂ የማፌዝ ምልክቶች፣ በቃል ወይም በፅሁፍ የሚገለጹ አስተያየቶች፣ ወይም ለሌሎች የሚያሳዩት ስነምግባር (ለምሳሌ:- የቃል ስድብ፣ መራገም፣ መላልሶ መጨቃጨቅ)። | | | | | | የማያቋርጥ እና ልምድ የሆነ እና ስነምግባሩ በትምህርት ላይ ተጽእና የሚያሣድር ንቀት፣ አለማክበር እንደ ረብሻ ሊቆጠር ይችላል። |
| | | የመምህራንን፣ የሰራተኞችን፣ ወይም የአስተዳዳሪዎችን መመሪያዎች በተደጋጋሚ መቃወም ወይም አለመቀበል። | | | | | |
| **ረብሻ** (704) | የትምህርት አካባቢን ሰላም በሚነሳ ተግባር መሳተፍ። | | | | | | ማስተጓጎል ማለት:- ማስተማርንና መማርን የሚያደናቅፍ፣ ሌሎችን ወይም የክፍል ውስጥ ትምሕርትን የሚያደናቅፍ ወይም የትምህርት ቤቱን እና/ወይም በትምሕርት ዲስትሪክቱ አሠራር ወይም ደህንነት ላይ ጣልቃ የሚገባ የተማሪ ባህሪ ነው። |
| | | መማር እና ማስተማርን በሚያደናቅፍ እና በቀጥታ የሌሎችን ደህንነት በሚያሰጋ ሁኔታ ከመለስተኛ እስከ ከባድ ተግባር ላይ መሳተፍ። | | | | | |
| | | | | በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ መፍጠር፣ ወይም ቀጣይነት ያለው የትምህርት ሂደቱን የማስተጓጎል ስጋት መፍጠር። | | | |
| | | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | | | |
| | | | ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያበረታታ ቋንቋን መጠቀም ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን መንዛት በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል። የቦርድ ፖሊሲ ACA፣ ፀረ መድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ይመልከቱ። | | | | |
| **የአለባበስ ሥርዓት/ኮድ** (706)<br>MCPS ደንብ JFA-RA፥ የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች | ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ የአለባበስ ስርአት የሚጥስ/የምትጥስ ተማሪ። | | | | | | |
| | | ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ የአለባበስ ስርአት ደጋግሞ የሚጥስ/የምትጥስ ተማሪ። | | | | | |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1 መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2 በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4 በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5 በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6 በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፤ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ትምህርት ማጭበርበር(801)**<br>*የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ MCPS ደንብ IKA-RA የሚያስከትለውን የውጤት አሰጣጥ መዘዞች ይመልከቱ። | የአካዳሚክ ሐቀኝነት የጎደለው ድርጊት የሚከተሉትን ያካትታል፥ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም (1) ስርቆት፣ በሌሎች የፈጠራ ስራ ወይም ሀሳብ እውቅና መውሰድ ወይም አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (AI)፣ (2) ማጭበርበር፣ ጥቅም ለማግኘት ወይም ጥቅም ለመስጠት ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መሥራት፣ ያልተፈቀደ ምንጭ ወይም AI አጠቃቀምን ጭምር፣ እና (3) የአስተማሪ ወይም የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማን በሐሰት ማስመሰል የመሳሰሉ የሐሰት ድርጊቶች ናቸው።<br>የትምህርት ችሎታ ምዘና/ፈተናዎችን ወይም ሌሎች ማርክ የተሰጠባቸው ስራዎችን መረጃዎች ማጋራት ወይም ማሰራጨት። | | | | | | |
| | | | | የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኮምፒውተር ኔትዎርክ ወይም ፈተናዎችን ያለፈቃድ መመንተፍ/መፈተሽ ወይም ሌላ ሰው ያለፈቃድ እንዲመነትፍ ማገዝ።<br>የትምህርት ችሎታ ምዘና/ፈተና የሚሰጥባቸውን መረጃዎች በተደጋጋሚ ወይም በስፋት ማሠራጨት። | | | |
| **ተገቢ ያልሆነ የግል ኤሌክትሮኒክስ መገልገያ አጠቃቀም (802)[4]**<br>MCPS እነዚህን "የግል ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች" ወይም "PMDs" ይላቸዋል።<br>MCPS ደንቦችን ይመልከቱ፡<br>- COG-RA የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች፣ IGT-RA፣ ለኮምፒውተር ሲስተም፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ፣ እና አውታረ መረብ አጠቃቀምን በሚመለከት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች፡-<br>ደህንነት፤ ILA-RA፣ ስለ ደህንነት እና ሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች የተደረጉ ግምገማዎች | የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) እና PMDs ደንቦችን በመጣስ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያን መጠቀም[4,5] | | | | | | ከ MCPS ንብረት የራቀ ሥፍራ ላይ የተፈጸመ የተማሪ ስነምግባር ጉድለት ከት/ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ሲኖረው፣ በአካልም ሆነ ቨርቹዋል የትምህርት አካባቢ ቢሆንም፣ ባህሪው በትምህርት ቤት እያሉ ሌሎች ተማሪዎችን የመጉዳት አደጋ ሲፈጥር፣ ወይም ምግባሩ በትምህርት አካባቢ ላይ የማደናቀፍ ድርጊት የሚያስከትል ከሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።<br>የተማሪ የውሂብ ግላዊነት ጥሰቶች፡- ተማሪዎች ማንኛውንም የግል መለያ መረጃዎችን (PII)፣ ሚስጥራዊ የዲስትሪክት መረጃዎችን፣ ወይም የጓደኞች ወይም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ሰራተኞችን የግል መረጃ ሠነዶችን (የትምሕርት ውጤት ወረቀቶችን፣ የእኩዮች የሥራ ውጤት ረቂቆችን ወይም የግል መልዕክቶችን ጭምር) ያልተፈቀደ የአርተፊሻል ፈጠራ AI መድረኮች ላይ መለጠፍ፣ ማሠራጨት ወይም ማቅረብ የተከለከለ ነው።<br>የተሳሳተ መረጃ ወይም የተዛባ መረጃ (ማለትም፡- የውሸት መረጃዎች) ማሰራጨት እና በድብቅ PMDs መጠቀም ለተማሪዎች ደህንነት ከፍተኛ አደጋ አለው። |
| | | ተማሪ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው/ከተሰጣት በኋላ MCPS ደንብ በመጣስ የግል ተንቀሳቃሽ/ሞባይል መሳሪያ መጠቀም ወይም | | | | | |
| | | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | | | |
| | | | የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ PMD መረጃን ማስተላለፍ፤ ግጭቶችን ሪኮርድ ለማድረግ፣ ወይም ከግጭት በኋላ የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል፤ ጸያፍ ወይም ስም አጥፊነት ነው፤ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ወይም MCPS ስራዎችን የሚያስተጓጉል፤ የትምህርት ሂደት ታማኝነትን የሚያጎድፍ፤ ወይም MCPS የኮምፒውተር ሲስተሞችን፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን (የትምሕርት ውጤት ወይም ሌሎች የተማሪ መረጃዎችን ጭምር) ደህንነትን የሚጥስ ድርጊት ማለት ነው። | | | | |
| | | | | MCPS ኔትወርክን ወይም ስራዎችን በሚያደናቅፍ መልኩ PMD መጠቀም፣ ሪኮርዶችን ለመቀየር ወይም የኤሌክትሮኒክስ ንብረትን ለማጥፋት PMD መጠቀምን ጨምሮ፣ ወይም MCPS በይነመረብን ለማወክ ከውጭ ፕሮክሲ ወይም ቨርቹዋል የመረጃ መስርሰር ጋር በማጣመር የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) መሳሪያን መጠቀም፣ ጉዳት የሚያስከትል አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (ማለትም፡- ውሸቶችን) መጠቀም፣ | | | |

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ስርቆት (803)**<br>MCPS ደንብ COB-RA፣የአደጋ ክስተቶችን ሪፖርት ስለማድረግ | | ከ $500 በታች ዋጋ ያለው ንብረት መውሰድ ወይም መቀበል። (ለተሰረቀ፣ ለጠፋ፣ ወይም ለተበላሸ ንብረት ካሳ ሊጠየቅ ይችላል።) | | | | | ዝርፊያ/የዘረፋ ሙከራ ወንጀል በአስቸኳይ ለህግ አስከባሪ አካላት ማሳወቅ ይገባል፣ እነርሱም በምርመራው ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ይሆናሉ።<br>ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ፣ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ከተማከሩ በኋላ፣ የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ከተማሪው(ዋ) የተሰረቀው ንብረት ዋጋ $1500 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ በሆነበት ማንኛውም ክስተት ወይም ተከታታይ ክስተቶች ላይ ምላሽ በመስጠት እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል።<br>ት/ቤቶች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማገናዘብ አለባቸው:-<br>• የተማሪው/ዋ ንብረቱን የመውሰድ አላማ<br>• በገንዘብ ሲተመን የንብረቱን ዋጋ<br>• ተማሪው(ዋ) ሆን ተብሎ የጠነሰሰ/ችው ሳይሆን፣ በአጋጣሚ ሁኔታ በወቅቱ የተፈፀመ ድርጊት ከሆነ<br>• ንብረቱ ዋጋ ያለውና ለመተካት ውድ መሆኑን ተማሪው ያውቅ እንደሆነ/ተማሪዋ ታውቅ እንደሆነ<br>• ንብረቱን መልሶ(ሳ) ከሆነ ወይም የተወሰደው ንብረት ተገኝቶ እንደሆነ |
| | | | | $500 ወይም ከዚያ በላይ ዋጋ ያለው ንብረት መውሰድ ወይም መቀበል። ቀደም ሲል የተፈጸመ የስርቆት እና/ወይም አስቀድሞ በታቀደ የተደራጀ ስርቆት ለመፈፀም የተሴሩ ክስተቶች። (ለተሰረቀ፣ ለጠፋ፣ ወይም ብልሽት ለደረሰበት ንብረት ካሳ መጠየቅ ይቻላል።) | | | |
| **ህግ መጣስ/መተላለፍ (804)**<br>*MCPS ደንብ COC-RA MCPS ንብረት ላይ መተላለፍ ወይም ሆን ብሎ ማወከን ይመልከቱ. | | | ከትምህርት ቤት ከታገደ(ች) ወይም ከተባረረ(ች) በኋላ በማንኛውም MCPS ንብረት ላይ ያለ ፍቃድ መገኘት። | | | | ሕገወጥ ድርጊት መፈጸም/ሆን ተብሎ የሚደረግ ረብሻ፣ ወይም ሌላ ሰው ሆን ብሎ ረብሻ እንዲፈጽም/እንዲፈጥር መርዳት፣ ከሌላ ጥፋት ጋር መተባበር፣ ማባባስ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃን ከፍ የሚያደርግ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የሌሎች ወንጀሎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም፤ መደባደብ፣ በተማሪ ወይም በሰራተኛ ላይ የሚፈፀም ጥቃት፣ ወይም ከአደንዛዥ እፅ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች። |
| | | | | | ረብሻ ለመፍጠር፣ ለመደባደብ፣ ሌላ ተማሪ ወይም ሰራተኛን ለማጥቃት፣ ወይም ንብረትን ለማውደም በማነሳሳት ጥሰት መፈጸም። | | |

[4]PMD ሶስት መለያ ባህሪያት አሉት:- 1) MCPS የመሳሪያው ባለቤትነት እንደሌለው ወይም አለመስጠቱን። 2) መሳሪያው መረጃዎችን ለመላክ እና ለመቀበል የኢንተርኔት፣ wi-fi ወይም ሴሉላር ግንኙነት የማግኘት፣ የመቀበል፣ እና የማስተላለፍ አቅም ካለው። 3) መሳሪያው ድምጽ እና ምስሎችን/ቪዲዮ መፍጠር እና መቅረጽ የሚችል ከሆነ፣

[5] የሌሎችን የንግድ ማስታወቂያ ወይም የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ መረጃ ከሆነ፣ የተማሪዎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ፣ ብልግና ወይም ስድብ ከሆነ፣ የትምህርት ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎችን የሚያስተጓጉል ከሆነ፣ ስራን የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያ (PMD) በመጠቀም ማስተላለፍ አይገባም።

# የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት) | ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፤ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፐሊን እርምጃ፤ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፤ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፐሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። | | | | | | | |
| **ንብረት ማውደም**<br>(806)<br>የሚከተሉትን ደንቦች ይመልከቱ፡- ደንብ COG-RA፣ የግል ሞባይል መሣሪያ/Personal Mobile Device ECC-RA፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ንብረት ማጥፋት ወይም ማበላሸት፤ እና ECG-RA፣ የመኪና ማቆሚያ መገልገያዎች እና የተማሪዎች ማሽከርከር፣ JNA-RB፣ ከተማሪዎች የፋይናንስ ክፍያዎችን መሰብሰብ | ድንገተኛ ጉዳት ማድረስ። | | | | | | የወንጀል መመዘኛዎችን ለማያሟሉ ክስተቶች፣ ትምህርት ቤቶች የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።<br>• የተማሪው/ዋ ንብረቱን የመውሰድ አላማ<br>• የንብረቱን ዋጋ በገንዘብ ሲተመን<br>• ተማሪው(ዋ) አስቀድሞ(ማ) ያሰበ(ች)ው/ያቀደ(ች)ው ሳይሆን በወቅቱ ባጋጠመ ድንገተኛ ሁኔታ ተነሳስቶ(ታ) የፈፀመ(ች)ው እንደሆን<br>• ንብረቱ ዋጋ ያለውና ለመተካት ውድ መሆኑን ተማሪው ያውቅ እንደሆነ/ተማሪዋ ታውቅ እንደሆነ<br>• ተማሪው(ዋ) ንብረቱን ያወደመበት/ያወደመችበት ምክንያት<br>በተጎጂው ዘር፣ ቀለም፣ ብሔር፣ ሃይማኖታዊ እምነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ ቤት አልባነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነትን ምክንያት በማድረግ የአንድን ሰው ንብረት የማበላሸት ሁኔታ ሲከሰት ወዲያውኑ ለሚመለከተው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት መደረግ አለበት።<br>የንብረት ጥፋት ወይም ንብረት የማውደም ተግባር ከተፈፀመ በአንድ ሰዓት ውስጥ ለትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ሪፖርት መደረግ አለበት እና COB-RA ደንብ መሠረት የሚከናወኑ ሂደቶችን መከተል አለባቸው። |
| | | | በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS)፣ በሰራተኞች፣ ወይም በተማሪዎች ንብረት ላይ የዋጋ ግምቱ ከ $500 በታች የሆነ ጉዳት ማድረስ። | | | | |
| | | | | በ MCPS፣ ሰራተኞች፣ ወይም ሌሎች ተማሪዎች ላይ ሆን ተብሎ $500 ወይም ከዚያ በላይ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ። | | | |
| | | | | አፀያፊ ቋንቋን መጠቀም፣ ወይም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ ማንነት ወይም በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያበረታቱ ምስሎችን ወይም ምልክቶችን መጠቀም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል። | | | |

# የባህሪ ማሻሻያ ጣልቃገብነት እርምጃዎች እና ትርጓሜዎች

| | |
|---|---|
| የስነምግባር ስምምነት/ኮንትራት | አወንታዊ የስነምግባር እርምት እርምጃዎች፣ ስልቶች፣ እና ድጋፎችን ለመስጠት በት/ቤት ሰራተኞች የተነደፈ መደበኛ እቅድ አማካይነት የተማሪን ተገቢ ያልሆነ ረባሽ ስነምግባር ማረም ያስፈልጋል። |
| የት/ቤት ካውንስለር/የሪሶርስ ስፔሻሊስት ክትትል | በት/ቤት ሰራተኞች አማካይነት ከት/ቤት ካውንስለር፣ ከሪሶርስ መምህር፣ የት/ቤት ሳይኮሎጂስት፣ የት/ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ  ወይም ከተማሪው ጋር የቅርብ ግንኙነት ካለው አሰልጣኝ ጋር ተማሪ እየተገናኘ ክትትል ይደረጋል። |
| በመማሪያ ክፍል የሚወሰድ እርምጃ<br>ምላሽ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች | ለአጭር ጊዜ ማስቆም፣ የአስተማሪና-የተማሪ ኮንፈረንስ፣ በጥሞና የማሰላሰል ጊዜ፣ ሚና መቀየር (ለምሳሌ፡- ሚና መጫወት)፣ የተቀመጠ(ች)በትን ቦታ ለውጥ ማድረግ፣ ወላጆችን ማነጋገር፣ ክፍል ውስጥ የተሳትፎ ሚና መገደብ፣ ወይም የይቅርታ ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግና የመሳሰሉትን በመጠቀም ተማሪዎች ባህርያቸውን እንዲያርሙ ማድረግ። |
| የማህበረሰብ አገልግሎት | ተማሪዎች ማህበረሰብን በሚጠቅሙ የተለያዩ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ወጥቤት ማሰራት፣  በት/ቤት ወይም በሌላም ስፍራ ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙበትን ቦታ ማፅዳት፣ ወይም አዛውንቶች የሚገለገሉበት ቦታ ላይ መርዳት)። ማሳሰቢያ፡- ለእንደዚህ አይነት ተግባራት የተመደቡ ሰዓቶች የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ተብለው አይቆጠሩም። |
| የግጭት አፈታት | (በት/ቤት የተመሰረተ ወይም ከውጭ የተቀናበረ) ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችላቸውን ስልቶች በመጠቀም ተማሪዎች ኃላፊነት እንዲወስዱ መርዳት። ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ የት/ቤት ሰራተኞች፣ እና ወይም ርእሰ መምህራን ግጭትና ንዴትን መቆጣጠር፣ በንቃት ማዳመጥ፣ እና ውጤታማ ግንኙነትን የመሳሰሉ ችግሮችን የመፍታት ክህሎቶችና ተክኒኮችን በሚያራምዱ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ። |
| በቁጥጥር ስር መዋል | አንድን ተማሪ ከትምህርት በፊት፣ በምሳ ወቅት፣ በእርፍት ጊዜ፣ ከትምህርት በኋላ፣ ወይም ቅዳሜና እሁድ ለተወሰነ ጊዜ መማርያ ክፍል ላይ በተለይ እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግ። ተማሪዎች ከመታገታቸው/በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ ከመደረጋቸው አስቀድሞ ትምህርት ቤቶች ለወላጆች/ለሞግዚቶች ለማሳወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። |
| ከት/ቤት ማስወጣት | ለወላጅ/ለአሳዳጊ በማሳወቅ ተማሪን  ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም 45 የትምህርት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ማገድ፣ ይህ ሊሆን የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡-<br>• የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ተማሪው/ዋ ከት/ቤት እንዲገለል የተወሰነው ጊዜ ከመጠናቀቁ አስቀድሞ የተመለሰ/ች እንደሆነ በሌሎች ተማሪዎች ወይም በሰራተኞች ላይ ጉዳት ማስከተሉ አይቀሬነቱን ሲያረጋግጥ፤<br>• የሱፐርኢንተንደንቱ ተወካይ ተማሪው(ዋ)ን ከትምህርት ቤት የማግለል ወቅት በተቻለ መጠን ማጠር ያለበትን ያህል ጊዜ ይወስናል፤ እና<br>• የተወገደ(ች)ው ተማሪ በስኬታማ ሁኔታ ወደ መደበኛ የአካዳሚ ፕሮግራሙ ሊመለስ/ልትመለስ ይችል ዘንድ ት/ቤቱ ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶች እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ ይሰጠዋል/ይሰጣታል። COMAR 13A.08.01.11(B)(2)(a-c) |
| ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ እና የእርምት እርምጃዎች እቅድ | ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ (FBA) (MCPS ቅጽ 336-64) ስለተማሪ አግባብነት የሌለው ትምህርትን የሚያደናቅፍ  ባህርይ አካሄድን መረጃ በመሰብሰብ የት/ቤት ሠራተኞች የተማሪን ባህርይ ለማረም ወይም ለመግራት የሚያስችሉ አቀራረቦችን ይወስናል። በመቀጠልም ለተማሪው(ዋ) የሚመጥን የስነምግባር ማስተካከያ ዕቅድ ለማዳበር (MCPS ቅጽ 336-65) መረጃው ጥቅም ላይ ይውላል። FBA በመጠቀም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ቡድን እና የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ተገቢውን የባህሪ ግቦችን እና ማስተካከያዎችን በማዘጋጀት የችግሩን መንስኤና ባህሪ ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት አማራጭ መፍትሔ ለመሻት ስልቶችን ያዘጋጃሉ። |
| በት/ቤት-የሚከናወን የባህርይ ማስተካከያ እርምጃ ጣልቃገብነት | አንድን ተማሪ በት/ቤት ህንፃ  ውስጥ ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም የማስወገድ እርምጃ ቢወሰድም ነገር ግን ተማሪው/ዋ የሚከተሉት እድሎች ይኖሩ(ሯ)ታል—<br>(i) በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የሚታይ ማሻሻል፤<br>(ii) ተማሪው/ዋ የአካል ጉዳተኛ ከሆነ/ች በህጉ መሰረት በተማሪው/ዋ IEP እንደተወሰነው ልዩ ትምህርትና የተዛመዱ አገልግሎቶችን ማግኘት፤<br>(iii) በመደበኛ የትምህርት ክፍል ሊያገኝ ከሚገባው/ልታገኝ ከሚገባት ትምህርት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ማግኘት፤ እና<br>(iv) በአሁኑ የትምህርት ፕሮግራማቸው ላይ እንደሚያደርጉት ሁሉ ከእኩዮቻቸው ጋር በተገቢው መጠን መሣተፍ። COMAR 13A.08.01.11(C)(2)(a) |
| ምክር የመስጠት ፕሮግራም | (በትምህርት ቤት መደበኛ ያልሆነ  የመከላከል እርምጃ) ለተማሪዎች በግል የመምክርና ስልጠና የሚሰጡ (ለምሳሌ፡- ካውንስለር፣ መምህር፣ ሠራተኛ፣ አብሮ የሚማር ተማሪ፣ ወይም የማህበረሰብ አባል) የግል፣ አካደሚክስ፣ እና ማህበራዊ እድገታቸውን በመምራት የሚረዱ ሰዎች ጋር ማቀናጀት። |

# የባህሪ ማስተካከያ እርምጃ ጣልቃገብነቶች እና ትርጓሜዎች (የቀጠለ)

| | |
|---|---|
| ከወላጅ ጋር መነጋገር | የልጆቻቸውን ባህሪ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማሳወቅ እና በትምህርት አውድ ላይ ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪን ለማረም የእነሱን እርዳታ መፈለግ። |
| የወላጅ/አሳዳጊ እና የተማሪ/መምህር ስብሰባ | ተማሪዎችን፣ ወላጅ/አሳዳጊዎችን፣ መምህራንን፣ የት/ቤት ሰራተኞችን፣ እና/ወይም ርእሰ መምህራንን ስለ ተማሪዎች ማህበራዊ፣ አካደሚያዊ፣ እና ከስነምግባር ጋር የተያያዙ የግል ጉዳዮችን በሚመለከቱ አይነተኛ የስነምግባር መፍትሄዎች ውይይቶች ማሳተፍ። |
| የእኩያ ጓደኞች የግልግል አገልግሎት | ስልጠና ያገኙ ተማሪዎች እንደ ገላጋይ/ሽማግሌ የሚያገለግሉበትና እኩዮቻቸው ግጭቶችን እንዲቋቋሙና መፍትሄዎችን በማዳበር እንዲያግዟቸው የሚደረግበት የግጭት መፍቻ ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ። |
| ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድ ማቅረብ | አንድን ተማሪ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት አስተዳዳራዊ እገዳ እንዲደረግ፣ እንዲባረር/እንድትባረር፣ አማራጭ ትምሕርት እንዲሰጠው/እንዲሰጣት ወይም ወደ ህግ አስከባሪ አካላት እንዲተላለፍና እንዲመክር ምክረሃሳብ ማቅረብ። |
| ወደ አማራጭ ትምህርት ማስተላለፍ | ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation IOI-RA ጋር በሚጣጣም መልኩ ተማሪ ወደ አማራጭ ፕሮግራም እንዲዛወር/እንድትዛወር ለት/ቤት አስተዳደር (አስተዳዳሪዎች) አስተያየት መስጠት፣ ለአማራጭ ፕሮግራሞች የምደባ ሂደት/አፈጻጸም፡፡ |
| ስለ አደንዛዥ እፆች መጥፎ አጠቃቀም ትምህርት እንዲያገኝ/እንድታገኝ ማስተላለፍ<br>የምክር/የካውንስሊንግ አገልግሎቶች | ከርእሰ መምህር/ት ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር፣ ወደ አካባቢ የጤና መምርያ ወይም ማህበረሰብን መሰረት ላደረገ አገልግሎት ከመጥፎ የዕፅ አጠቃቀም ጋር ለተያያዘ የምክር አገግሎት በት/ቤት ውስጥም ሆነ ከት/ቤት ውጭ አገልገሎቶች ወደሚሰጡበት ተማሪዎችን መምራት። |
| ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅት መምራት/ማስተላለፍ | ከርእሰመምህር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር ከትምህርት ሠዓት በኋላ-ፕሮግራም፣ የግል ወይም የቡድን የምክር አገልግሎት፣ የአመራር እድገት፣ ግጭቶችን ማስታረቅ፣ እና/ወይም ግላዊ ስልጠና ወደሚያካትቱ የተለያዩ አገልግሎቶች ተማሪዎችን መምራት። |
| የጤና/የአእምሮ ጤና አገለግሎት እንዲሰጥ ማስተላለፍ | ከርእሰመምህር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር፣ ምክርና ግምገማ እንዲደረግላቸው የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን ወደ ት/ቤት የጤና አገልግሎት ክፍል ወይም ወደ ማህበረሰብ የጤና እና የአእምሮ ጤና ክሊኒኮች ወይም ሌሎች አገልገሎቶች መምራት/መላክ። ተማሪዎች ተገቢ ወዳልሆኑ ወይም ረብሸኛ ስነምግባሮች ወይም በትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያደርጉ አሳሳቢ ጉዳዮቻቸውን ከሌሎች ገንቢ ምክር ለማግኘት በግል እንዲያጋሩ እና በግል የሚፈታተኗቸውን ነገሮች ለመቋቋም የሚያግዙዋቸውን ቴክኒኮች እንዲማሩ ይበረታታሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ቁጡነትን መቆጣጠር እና መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ የባህሪ መስተጓጎል መግራትን ሊያካትቱ ይችላሉ። |
| ወደ ተማሪ ማስተላለፍ/ሪፈራል<br>የድጋፍ ሰጪ ቡድን | ከርእሰመምህር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር፣ የተማሪን ውጤት ለማሻሻል የመከላከያና የእርምት ቴክኒኮችና አማራጭ ስልቶችን ለማዳበር የት/ቤት አማካሪዎች፣ የተማሪ ፐርሶኔል ሰራተኞች፣ መምህራን፣ ርእሰመምህራን፣ የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች (social workers)፣ የጤና አገልግሎቶች፣ የጤና ክሊኒክ ሰራተኞች፣ የት/ቤት ሳይኮሊጂስቶች፣ እና የውጭ ተቋም ተወካዮችን ሊያጠቃልል የሚችል የድጋፍ ቡድን የተማሪውን ጉዳይ ከሚከታተለው ሰው (case manager) ስር መመደብ። የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን ባዘጋጀው እቅድ አፈጻጸም የተማሪ ባህርይ/ስነምግባር ካልተሻሻለ፣ ቡድኑ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS ደንብ IOI-RA፣ ጋር በተጣጣመ መልኩ የምደባ አማራጭ ይጠይቃል፣ ለአማራጭ ፕሮግራሞች የምደባ ሂደት። |
| ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ከሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች መወገድ /ከተጠቃሚነት መታገድ | ከርእሰ መምህር ወይም ተወካይ ጋር በመነጋገር፣ ተማሪ ከከሪኩለም ትምህርት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍን መብት ለመንፈግ/፣ ስፖርት እና ክለቦችን፣ ወይም ተማሪ በት/ቤት ሁነቶች ላይ ወይም እንቅስቃሴዎች (እንደ መስክ ጉዞ ወይም በት/ቤት ዳንስ መሳተፍን የመሳሰሉ) ላይ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ ማገድ። የስነምግባር ጥሰቱ የዚህን አይነት እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ከሆነ፣ ለተጓደለው እንቅስቃሴ ከተቻለ በተማሪው(ዋ) የተከፈሉ ገንዘቦች ካሉ መመለስ አለባቸው። |
| የካሳ ክፍያ | በተማሪው(ዋ) ስነምግባር ምክንያት በሌሎች ላይ ለደረሰ ጥፋት፣ ብልሽት፣ ወይም ጉዳት ተማሪው(ዋ) ካሣ እንዲከፍል/እንድትከፍል መጠየቅ። ካሳው በገንዘብ ወይም ተማሪውን (ተማሪዋን) በት/ቤት ፕሮጀክት ስራ እንዲሰራ በመመደብ፣ ወይም በሁለቱም ሊከናወን ይችላል።<br><br>COMAR 13A.08.01.11(D) ድንጋጌ መሰረት አንድ ተማሪ የስቴት ወይም የአካባቢ ህግን ወይም መመሪያን ከጣሰ(ች) እና ጥሰቱ በተፈጸመበት ጊዜ ወይም ምክንያት የትምህርት ቤቱን ንብረት ጉዳት ከደረሰበት ወይም ንብረት ዋጋው በእጅጉ ከቀነሰ። ወይም በወቅቱ በትምህርት ቤት ንብረት ላይ የነበረ የሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ከደረሰ፣ ርእሰ መምህሩ ከተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ግለሰቦች ጋር በጉዳዩ ላይ ኮንፈረንስ ካደረጉ በኋላ እንዲመልሱ ይጠይቃሉ። የገንዘብ ካሳ $2,500 ወይም ከንብረቱ የገበያ ዋጋ ግምት ወይም ከሁሉቱ አነስተኛውን ዋጋ የሚበልጥ መሆን የለበትም። |

| | |
|---|---|
| የስነምግባር ተሐድሶ እርምጃዎች | (በትምሕርት ክፍል ውስጥ ወይም በልዩ ባለሙያ የሚተገበር) የስነምግባር ተሐድሶ እርምጃዎች አወንታዊ የትምህርት ቤት ሁኔታን ለመጠበቅ እና ተገቢ ማህበራዊ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዋቀረ አቀራረብን በመንደፍ በቀዳሚነት (proactively) ይተገበራሉ። የስነምግባር ተሐድሶ እርምጃ አቀራረቦች በአንድ ክስተት ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት፣ በሰው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ጭምር፣ ለመለየት እና ችግሩን ለመፍታት እና ጉዳቱን ያደረሰ(ች)ው ተማሪ ጭምር ከሁኔታው እንዲረጋጋ እና ባህርይ እንዲያስተካክል በማቀድ የተነደፉ የስምግባር ማስተካከል ጣልቃ ገብነቶችን፣ እና የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይተገብራሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት MCPS ደንብ JGA-RB፣ እገዳ እና ማባረርይመልከቱ። |
| የትምህርት ቤት - ወይም የማህበረሰብ ስብሰባ | ተማሪዎችን፣ የት/ቤት ሰራተኞችን እና በግጭቱ የተሳተፉ ሌሎችን በርእሱ ለመወያየት፣ ጉዳዮችን ለመፍታት፣ እና መፍትሄዎች ለማቅረብ መሰብሰብ (ለምሳሌ፡- “Daily Rap” “Morning Meetings”)። |
| ዳግም ወደ ትምህርት ቤት ስለመመለስ የሚደረግ (የመግቢያ) ስብሰባ | ተማሪው(ዋ) የዲሲፕሊን ቅጣት (ከት/ቤት እገዳ) እርምጃ ከተወሰደበ(ባ)ት በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ/እንድትመለስ በሚጠበቅበት ቀን ከርዕሰ መምህር/ከረዳት ርእሰ መምህር ጋር ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ መግቢያ (የመግቢያ) ስብሰባ እንደሚደረግ ይጠበቃል። ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ መግቢያ (የመግቢያ) ስብሰባዎች ተማሪ ለረጅም ጊዜ ከትምሕርት ቤት መቅረት ወይም በሌሎች ምክንያቶችም ለብዙ ቀናት የትምህርት ክትትል ካመለጠው/ካመለጣት በኋላ ወደ ትምህርት ተመልሶ የመግባት ስብሰባዎች ሊደረጉ ይችላሉ። |
| እገዳ (ለአጭር ጊዜ ከት/ቤት ውጭ እንዲቆይ/እንድትቆይ መወሰን) | አንድ ተማሪ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት እስከ 3 የትምህርት ቀናት ድረስ ከትምህርት ቤት ከተባረረ(ች)፣ ነገር ግን ከዚያ በላይ መሆን የለበትም፣ ለወላጅ/ለአሳዳጊ ማሳወቅ ያስፈልጋል። |
| ከትምሕርት ቤት እንዲታገድ/እንድትታገድ መወሰን (ለረጅም ጊዜ፣ ከት/ቤት ውጭ) | ለወላጅ/አሳዳጊ እያስታወቁ፣ በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያቶች የአንድ ተማሪ ከት/ቤት 4 እስከ 10 የትምህርት ቀኖች በርእሰመምህሩ/ሯ መታገድ መወሰን። |
| ከትምህርት ክፍል ማስወጣት<br><br>(ለቀሪው የትምህርት ሰዓት) | በርእሰመምህር ውሳኔ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት ለወላጅ/ለአሳዳጊ በማሳወቅ ለቀሪው የትምህርት ቀን ተማሪን ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ተማሪው(ዋ) በሚቀጥለው የትምህርት ቀን ተመልሶ(ሳ) ወደ ት/ቤት እንዲመጣ/እንድትመጣ ይጠበቃል። ተማሪው(ዋ) ወደ ትምህርት ቤት በሚመለስበት/በምትመለስበት ቀን ከርዕሰ መምህሩ/ከረዳት ርእሰ መምህሩ እና ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ከተማሪው(ዋ) ስለሚጠበቅ ባህሪ ለመነጋገር የተማሪ ዳግም ወደ ት/ቤት የመመለስ ስብሰባ መደረግ አለበት። የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደባቸው ተማሪዎች በመደበኛ የትምህርት ሰዓትም ሆነ ከዚያ ውጭ MCPS በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ወይም ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ወይም መገኘት አይችሉም። ይህ የአትሌቲክስ ዝግጅቶችን፣ ክለቦችን፣ ስፖርታዊ ትርኢቶችን፣ ወይም ሌሎች ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶችን ያካትታል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። |
| (በት/ቤት ውስጥ) ከክፍል ውጭ እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግ | ለወላጅ/አሳዳጊ እያስታወቁ፣ በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያቶች የአንድ ተማሪ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከወቅታዊ የት/ቤት ፕሮግራም እስከ 10 ቀናት፣ ነገር ግን ከዚያ ለማይበልጡ ቀኖች በት/ቤቱ ርእሰመምህር መታገድ ይችላል። ተማሪዎች በመደበኛ የትምህርት ሰዓት ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ MCPS በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ወይም ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ወይም መገኘት አይችሉም። ይህ የአትሌቲክስ ዝግጅቶችን፣ ክለቦችን፣ የስፖርት ትርኢቶችን ወይም ሌሎች ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶችን ያካትታል፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። |
| እገዳ (ለረጅም ጊዜ ከት/ቤት ውጭ ማቆየት) | ለወላጅ/ሞግዚትበማሳወቅ ተማሪን ከመደበኛ የትምህርት ቤት ፕሮግራም (11 እስከ 44 የትምህርት ቀናት መካከል የሚደርስ) ለተራዘመ ጊዜ ማስወገድ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች/ምክንያቶች ብቻ ሊደረግ ይችላል፡-<br><br>የትምሕርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ የሚከተሉትን ሲያረጋግጥ፡-<br><br>ሀ/ የተወሰነው የእገዳ ጊዜ ከመፈፀሙ በፊት የተማሪው/ዋ ወደ ት/ቤት መመለስ በሌሎች ተማሪዎችና ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ፤ ወይም<br><br>ለ/ ተማሪው/ዋ ያደረገው/ችው ተደጋጋሚና ከፍተኛ ረብሻ በሌሎች ተማሪዎች የትምህርት ሂደት ላይ መጠነ ሰፊ እክል በሙሉ የትምህርት ቀን ላይ ፈጥሯል፣ እንዲሁም ሌሎች መተግበር የሚቻሉ እና ተገቢ የስነምግባርና የዲሲፕሊን ማስተካከያዎች በሙሉ ተሞክረዋል ተብሎ ከታመነ።<br><br>የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ የእገዳውን ወቅት እጅጉን ሊያጥር ወደሚቻልበት ጊዜ ይቀንሳል።<br><br>የተማሪው(ዋ)ን ወደ መደበኛ አካዴሚያዊ ፕሮግራም በስኬት እንዲመለስ/እንድትመለስ ለማድረግ ት/ቤቱ ለተወገደ(ች)ው ተማሪ ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶች እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ ያቀርብለ(ላ)ታል። ተማሪዎች በመደበኛ የትምህርት ሰዓትም ሆነ ከዚያ ውጭ MCPS በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ወይም ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ወይም መገኘት አይችሉም። ይህ የአትሌቲክስ ዝግጅቶችን፣ ክለቦችን፣ ስፖርታዊ ትርኢቶችን ወይም ሌሎች ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶችን ያካትታል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። |
| ከመማርያ ክፍል በጊዜያዊነት መወገድ | ተማሪዎችን በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራማቸው ለአንድ፣ ነገር ግን ከዚያ ለማይበልጥ፣ የትምህርት ፔርየድ ማገድ። |

# የተማሪ የሥነ ምግባር ደንብ እና የልዩ ትምህርት መስፈርቶች

## የቦርድ ደንብ JGA-RA፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እገዳ እና መባረር

### የመገለጫ ውሳኔ እና 45-ቀናት IAES

*ፈጣን መመሪያ*

IEP ቡድን ስብሰባዎች እና ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ዝግጅቶች • ለ MCPS መሪዎች ስርዓት አቀፍ ማጣቀሻ

### የሥነ ምግባር ደንብ—የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የዲሲፕሊን እርምጃዎች (SWD)

አጭር መግለጫ፡- የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ስኬትን ይጠብቃሉ፣ ስለሆነም ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹ እና ፍትሃዊ የትምሕርት አውድ እንዲኖር ለማድረግ ቁርጠኛ ናቸው።

በግላዊ ሁኔታ የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች (IEPs) ያላቸው ተማሪዎች ልክ እንደ ሌሎቹ ተማሪዎች ተመሳሳይ የተማሪ የሥነ ምግባር ደንቦችን እና የባህሪ ደረጃዎችን እንዲጠብቁ ይደረጋ። ይሁን እንጂ፣ የፌዴራል እና የስቴት ሕግ የዲሲፕሊን መርኆች በተማሪው(ዋ) የአካል ጉዳት እና በባህሪው(ዋ) መካከል ያለውን ግንኙነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ መስፈርቶችን በአግባቡ እንዲያጤኑ ያደነግጋል።

እንደዚህ አይነት እንክብካቤዎች/ጥበቃዎች የስነምግባር ጉድለትን ለመሸፈን ሳይሆን፤ ይልቁንም የሚወሰዱት እርምጃዎች/ውሳኔዎች/ ከትምህርት ሁኔታ ጋር የሚስማሙ፣ ከህጋዊነት ጋር የሚሣለጡ፣ እና ከተማሪዎች ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳሉ።

### የባህርይ መገለጫ ደንቡን መረዳት

— ለማድረግ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድ የባህርይ መገለጫ ግምገማ (MDR)ማድረግ ያስፈልጋል

- 10 የትምህርት ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ማስወገድና የቦታ ምደባ ለውጥን የሚያስከትል ከሆነ፤ ወይም
- በፌዴራል እና በስቴት ሕግ መሠረት የሚፈቀዱ የተወሰኑ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መውሰድ ካስፈለገ፤

በዚህ ሂደት፣ IEP ቡድን —ለመወሰን ያሉትን መረጃዎች መገምገም ይኖርበታል፡

1. ድርጊቱ የተከሰተበት ምክንያት ከተማሪው(ዋ) የአካል ጉዳተኝነት ጋር ቀጥተኛ እና ጉልህ ግንኙነት ያለው መሆኑን፤ ወይም
2. ድርጊቱ የተማሪው(ዋ)ን IEP ተግባራዊ አለማድረግ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን ወይም አለመሆኑን።

ከዚያ በኋላ ቡድኑ IDEA፣ COMAR እና አግባብነት ካለው የአፈጻጸም መስፈርቶች ጋር በማገናዘብ ተገቢ የሆኑ ቀጣይ እርምጃዎችን እና የድጋፍ ተግባራትን ይወስናል።

### ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ዝግጅት (IAES)

በፌዴራል እና በስቴት ህግ በተደነገጉ የተወሰኑ ሁኔታዎች፣ IEP ቡድን እስከ 45 ቀናት ድረስ በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቅንብር (IAES) ለመመደብ ይችላል።

IAES ማለት—

- የጊዜያዊ ትምህርት ምደባ፣
- የትምህርት አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን ተደራሽነት ለመጠበቅ የተነደፈ ቅንብር፣
- ወደ IEP ግቦች ቀጣይነት ያለው እድገትን እና በትምህርቱ ላይ መሳተፍን የሚያመቻች ምደባ፣ እና
- በርእሰ መምህር ውሳኔ የተወሰኑ ህጋዊ ሁኔታዎችን እና የአፈጻጸም መስፈርቶችን በማገናዘብ ብቻ የሚወሰድ እርምጃ።

የቦታ ምደባ ውሳኔው በግለሰቡ(ቧ) ሁኔታ የተዘጋጀ እና በተማሪዎች ፍላጎቶች፣ ባሉት መረጃዎች፣ እና በሚመለከታቸው ህጋዊ መስፈርቶች ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው።

# የተማሪዎች የሥነ ምግባር ደንብ እና አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም መስፈርቶች

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS)፣ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች ማለት፡- በመደበኛ የትምህርት ቤት ሁኔታ ውስጥ ፍላጎታቸው በተሳካ ሁኔታ የማይሟላላቸው ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተዘጋጁ ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ናቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች በመደበኛ የትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ ከሚሰጠው የትምህርት አገልግሎት በተለይ ተጨማሪ የትምህርት፣ የባህሪ፣ የማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ድጋፎችን ይሰጣሉ።

## አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞችን መረዳት

MCPS አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚከተሉት ሁኔታዎች ላጋጠማቸው ተማሪዎች ቀጣይነት ያለው የትምሕርት ድጋፍ አካል ናቸው፡-

1. ትምህርት ለመማር የሚያዳግቱ ጉልህ ችግሮች
2. ሥር የሰደደ ትምህርት ቤት የመከታተል ችግሮች
3. የባህርይ ተግዳሮቶች
4. ማህበራዊ-ስሜታዊ ወይም የአእምሮ ጤንነት ስጋቶች
5. በመካከለኛ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስኬታማ የመሆን ችግር ያጋጠማቸው

አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች እንደ ብሌር ጂ. ኢዊንግ ማዕከል /Blair G. Ewing Center በመሳሰሉ አማራጭ የልዩ ትምህርት ማእከሎች ላይ ይሰጣሉ። ግቡ ተማሪዎች በትምህርት ላይ እንዲቆዩ፣ ክሬዲት እንዲያገኙ፣ ባህሪያቸውን እንዲያሻሽሉ፣ እና ት/ቤት የመገኘትን ሁኔታ እንዲያሻሽሉ፣ እና በመጨረሻም እንዲመረቁ ለመርዳት ነው።

## አንድ ተማሪ ለአማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንዴት ብቁ ይሆናል?

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤት (MCPS) ተማሪ ልክ እንደ ማግኔት ወይም የልዩ ትምህርት ፕሮግራም በቀጥታ አይያመለክትም/አታመለክትም። ይልቁንም፣ MCPS የተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት የተለያዩ የትምሕርት አቀራረብ ጣልቃ ገብነቶችን እና ድጋፎችን መጀመሪያ እንዲሞክር ይደረጋል። ትምህርት ቤቶች ተማሪው(ዋ)ን ወደ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ከማስተላለቸው በፊት የተማሪው(ዋ) የስነምግባር ባህሪ ክብደት በትምህርት አካባቢ ላይ ፈጣን ለውጥ ለማድረግ የሚያስገድድ ካልሆነ በስተቀር የስነምግባር ተሐድሶ እርምጃዎችን/አቀራረቦችን እና የባህርይ ማሻሻል የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የመሳሰሉ ተከታታይ የማስተማሪያ እና የባህሪ ማስተካከል ስልቶችን እንዲጠቀሙ ይጠበቅባቸዋል።

ወደ ተለየ ውሳኔ ሊያመሩ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

1. የትምሕርት ድጋፍ የመስጠት ጣልቃ ገብነት ቢኖርም ትምህርት ላይ በተደጋጋሚ መውደቅ
2. ጉልህ የሆኑ የባህሪ ተግዳሮቶች
3. በትምህርት ቤት ስራ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ-ስሜታዊ ተግዳሮቶች
4. መደበኛው የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎቶች የማያሟላ ከሆነ

## ወላጆች ተማሪ ልጃቸው ወደ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንዲገባ/እንድትገባ መጠየቅ ይችላሉ?

ወላጆች ስለጉዳዩ ከተማሪው(ዋ) ካውንስለር፣ ከአስተዳዳሪ ወይም ከትምህርት ቤት የድጋፍ ቡድን ጋር መወያየት እና አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ግምገማ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆን መጠየቅ ይችላሉ። ሆኖም፣ የወላጅ ጥያቄ ብቻውን ተማሪው(ዋ)ን ብቁ አያደርግም። MCPS የምደባ ውሳኔ የሚሰጠው የሪፈራል እና የግምገማ ሂደቱን በማገናዘብ ነው።

## አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንደ ልዩ ትምህርት ይቆጠራል?

አማራጭ ፕሮግራሞች ከልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የተለዩ ናቸው። MCPS ተገቢ የትምህርት ምደባ መሆኑን ከወሰነ፣ IEP ያላቸው ወይም የሌላቸው ተማሪዎች አማራጭ ፕሮግራም መከታተል ይችላሉ። በፌዴራል እና በስቴት ህጎች እና የቦርድ ደንብ JGA-RA፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከትምሕርት እገዳ እና መባረርድንጋጌ መሠረት IEP ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይደነግጋል። (ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የተማሪ የሥነ ምግባር ደንብ እና የልዩ ትምህርት መስፈርቶችን ገጽ 31 ላይ ይመልከቱ።)

# የአፈጻጸም ሂደት ፕሮቶኮል

## በትምህርት ቤት ደረጃ የሚደረግ የምርመራ ሠንጠረዥ

### ስለተፈጠረ ክስተት ማሳወቅ

- ስለ አንድ ክስተት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር እንዲያውቅ መደረግ አለበት
- እንደ አስፈላጊነቱ DSLI ዳይሬክተር እና የክላስተር ደህንነት አስተባባሪን ያነጋግሩ

### ደህንነትን ያረጋግጡ

- በክስተቱ የተሳተፉ ተማሪዎችን መለየት ያስፈልጋል
- አስፈላጊ ከሆነ የሕክምና እርዳታ ይሰጥ
- አስፈላጊ ከሆነ በሥፍራው መቆየት፣ ከለላ መያዝ፣ እና መቆለፍ፣ ይተገበራል

### መቅደም ያለባቸው ነገሮች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል

- በተማሪ መብቶችና ኃላፊነቶች ድንጋጌ መሠረት የድጋፍ እርምጃዎችን እቅድ ለመተግበር

### የተማሪ መግለጫዎችን ይሰብስቡ

- ከእያንዳንዱ ተሳታፊ መግለጫዎችን በተለይ ይሰብስቡ፦
  - ከተማሪዎች
  - ከሠራተኞች
  - ከደህንነት ጥበቃ
- MCPS ቅጽ 230-45፣የተማሪ የክስተት መግለጫ ቅጽ ይጠቀሙ

### የዲሲፕሊን እርምጃ የሚወሰድባቸው ተማሪዎች የምስክርነት መግለጫ የመስጠት እድል ሊሰጣቸው ይገባል

### በዓላማ ላይ ያተኮረ እርምጃ

- ምስክሮችን መጠየቅ እና ቃለ መጠይቅ ማድረግ
- ክስተቶቹ የተፈጸሙበትን የጊዜ ሂደት ማዘጋጀት
- MCPS የፍተሻ እና መውረስ ሂደቶችን መከተል

### ያሉትን ማስረጃዎች ማሰባሰብ

- የቪዲዮ ማስረጃ
  - የደህንነት ካሜራዎች
  - የት/ቤት አውቶቡስ
  - የእጅ ስልኮች
- የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች
  - MCPS ኮምፒውተሮች
  - በቅጽበት የተነሱ ምስሎች

### የተገኘውን ውጤት በመመርኮዝ ውሳኔ መስጠት

- የተማሪ ሥነ ምግባር ደንብ በሚደነግገው መሠረት የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ
- አስፈላጊ ከሆነ፣ የባህሪ ስጋት ግምገማ ቡድን (BTAT) ስብሰባ ማድረግን ግምት ውስጥ ያስገቡ፣
- የስነምግባር ተሐድሶ እቅድ ማዘጋጀት

### ግንኙነትን/ኮሙኒኬሽን የሚመለከቱ ውሳኔዎች

- ጉዳዮች
  - የእገዳ ደብዳቤ
  - የትምህርት ቤት-ማህበረሰብ ደብዳቤ*
- ስለ እገዳው ለ ---ማሳወቅ
  - ለአስተዳደር ቡድን
  - ለተማሪ ጉዳዩ ሠራተኛ
  - ለት/ቤት የቁጥጥር ጸሐፊ
  - ለት/ቤት ደህንነት ጥበቃ
  - ለመምህራን

### ለሪከርድ ክፍል

- ክስተቱን በፋይል/ሲነርጂ ላይ መመዝገብ እና በየጊዜው ማዘመን ያስፈልጋል
- ስለ 10&E ጥያቄዎች ለተማሪዎች የስነምግባር እና ይግባኝ ክፍል ማሳወቅ

### በሰነድ/ሲነርጂ መመዝብ አለበት

### የቀጣይ እርምጃዎች እቅድ

- የድጋፍ እርምጃዎች ዕቅድ
- የካውንስሊንግ ድጋፍ
- ወደ SWBT ማስተላለፍ /ሪፈራሎች
- የስነምግባር ተሐድሶ እርምጃ እቅድ መተግበር
- ዳግመኛ ወደ ት/ቤት የመግባት እቅድ
- ተማሪን የመቀበል ስብሰባ

## የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና የተማሪ ባህሪ ማስተካከያ እርምጃ፣ ደህንነትን፣ እና ጤንነትን የሚመለከቱ MCPS ደንቦች

ፖሊሲ ACA፣ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ፣ ፍትሃዊ፣ እና የዳበረ ባህል

ፖሊሲ ACF፣  ስለ ተማሪዎች ወሲባዊ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ

ፖሊሲ ACI፣  ስለ ሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ

ፖሊሲ COA፣ ስለ ተማሪዎች ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም

ፖሊሲ EEA፣ ስለ ተማሪዎች መጓጓዣ

ፖሊሲ IGN፣ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ መጠቀምን መከላከል

ፖሊሲ IGA፣ ስለ ተማሪዎች የማህበራዊ ስሜታዊ እና የአእምሮ ጤንነት  ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

ፖሊሲ JFA፣ ስለ ተማሪዎች መብቶችና ሀላፊነቶች

ፖሊሲ JGA፣ ስለ ተማሪዎች ሥነምግባር ባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች፣ ደህነነት፣ እና ጤናማ ቁመና ዕቅድ

ፖሊሲ JHF፣ ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት

ደንብ ACA-RA፣ ፀረ-መድልዎ፣ ፍትኃዊነት፣ እና የባህል ብቃት

ደንብ ACF-RA፣ ታይትል IX የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ስለ ተማሪዎች ጾታዊ ጥቃት ምርመራ

ደንብ ACG-RB፣ የስነምግባር ተሐድሶ 1973 ሰክሽን 504 መሰረት ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ተስማሚ መገልገያዎችና ማሻሻያዎች

ደንብ COA-RA፣  ስለ ባህርይ ስጋት ግምገማ

ደንብ COC-RA፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን ንብረት ማውደም/ማበላሸት/ንብረት ላይ የሚፈፀም ጥሰት እና ረብሻ

ደንብ COE-RA፣ የጦር መሳርያዎች

ደንብ COF-RA፣ አልኮሆል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ንብረት ላይመጠቀም

ደንብ COG-RA, የግል ተንቀሳቃሽ/ሞባይል መገልገያዎች

ደንብ ECC-RA፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ንብረት  መጥፋት ወይም መበላሸት

ደንብ EEA-RA, የተማሪዎች መጓጓዣ

ደንብ EEB-RA, የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች አውቶቡሶችን በጥንቃቄ ማሽከርከር

ደንብ IGO-RA፣ የአልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚያካትቱ አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ ስለመጠቀም ክስተት መመሪያ

ደንብ IGT-RA፣ የኮምፒውተር አጠቃቀም፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎች፣ እና የመገናኛ አውታረ መረብ ደህንነትን በሚመለከት የተጠቃሚ ሀላፊነቶች

ደንብ ILA-RA፣ ስለ ደህንነት እና ሪፖርት የማድረግ አስፈላጊነት መስፈርት

ደንብ IOI-RA, ስለ አማራጭ የትምሕርት ፕሮግራሞች ምደባ ሂደት

ደንብ JEA-RA፣ የትምህርት ክትትል

ደንብ JEE-RA, የተማሪ ዝውውሮች እና አስተዳደራዊ ምደባዎች

ደንብ JFA-RA, የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች

ደንብ JGA-RA፣ የተማሪ ባህሪ ማስተካከያ እርምጃ ጣልቃገብነት

ደንብ JGA-RB, ከት/ቤት እገዳና ስንብት

ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች እገዳና ስንብት

ደንብ JGB-RA፣ ፍተሻ እና መውረስ

ደንብ JHF-RA፣  የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት

ደንብ JHG-RA፣ ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የጥፋት ወይም ህገወጥ የቡድን ስነምግባርን መከላከል

ደንብ JNA-RB፣ ከተማሪ የገንዘብ ክፍያ/የፋይናንስ ግዴታዎችን መቀበል/መሰብሰብ

ደንብ JPC-RA፣ ለተማሪዎች የመድሃኒት አሰጣጥ መመሪያ

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜጎች መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Department of Student Conduct and Appeals የተማሪ ስነ-ምግባር እና ይግባኝ ክፍል<br>የተማሪዎች ደህንነት እና ደንብ የማክበር ቡድን Student Welfare and Compliance Team<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Department of Student Conduct and Appeals, Title IX Team የተማሪዎች ሥነ ምግባር እና ይግባኝ ክፍል፣ ታይትል IX ቡድን<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኤፕረል 2026

ሕትመት፡- Division of Communications
1229.26 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 6/26 • ?
የቅጂ መብት፡- Copyright © 2026 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland